የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ፍተሻ (በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አማርኛን የማስተማር ዘዴ (TeAm) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ጥላሁን ከበደ

ጥር፣ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር ፍተሻ (በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል አማርኛን የማስተማር ዘዴ (TeAm) ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በ

ጥላሁን ከበደ

ጥር፣ 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በተመረጡ ሶስት የመንግስት ተምህርት ቤቶች

በ

ጥላሁን ከበደ

በቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

የፊተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ስም ፊርማ

[illegible]

አማካሪ

[illegible]

ፈታኝ

ምስጋና

ይህ ጥናት በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ ሠፊ ጊዜያቸውን ሰውተው አቅጣጫ በማስያዝና በማስተካከል ለተባበሩኝ አማካሪዬ አቶ ጌታቸው እንዳላማው (ረዳት ፕሮፌሰር) ጥልቅ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ፡፡ እንዲሁም ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የሮቢት፣ የቆቦና የወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የአስተዳደር ሰራተኞችን አመሰግናለሁ፡፡

መተዋወቅ የአጋጣሚ ነገር ቢሆንም አብሮ ለመኖር ግን ፍቅር ያስፈልጋልና ከተገናኘንበት ጊዜ ጀምሮ በቀናነት አንዳችን የአንዳችንን ስራ በማየትና በመገማገም ያደረግነው ጥረት ይኸው ዛሬ ተሳካ፤ ውድ ጓደኞቼ አማረ ተሾመ፣ በላይነህ ሐይሌ፣ በጎሰው የሸዋስ፣ ከድር ጋሻው፣ ሙሉቀን ንጋቱ፣ ተመስገን ታደሰና አብርሃም ገ/ዩሃንስ በጣም አመሰግናችኋለው፡፡ በመጨረሻም ትምህርቴን ጀምሬ እስክጨርስ በገንዘብና በቁሳቁስ ለተባበረችኝ ለእህቴ ሙሉ ከበደና ለመላው ቤተሰቦቼ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ማውጫ

ርእስ ገፅ

ምስጋና i

ማውጫ ii

የሰንጠረዥ ማውጫ vi

አጠቃሎ viii

ምዕራፍ አንድ መግቢያ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አላማ 4

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ 5

1.4 የጥናቱ ገደብ 5

ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት 7

2.1 የማዳመጥና የንግግር ክሂል ምንነት 7

2.1.1 የማዳመጥ ምንነት 7

2.1.2 የንግግር ክሂል ምንነት 10

2.2. የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት 12

2.3 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ አስፈላጊነት 15

2.4 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች 18

2.4.1 ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ 18

2.4.2 ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ 19

2.5 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚያግዙ ስልቶች 20

2.6 የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት የመምህሩ ሚናና ተግባር 22

2.7 የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ለክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው አስተዋፆ 25
2.7.1 መርህ ትምህርት 25
2.7.2 የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሀፍ 25
2.8 የቀደምት ስራዎች ቅኝት 26
ምዕራፍ ሦስት የጥናቱ ዘዴ 29
3.1 የናሙና መረጣና የተተኳሪዎች አወሳሰድ 29
3.1.1 የክልልና የዞን አመራረጥ 29
3.1.2 የትምህርት ቤት አመራረጥ 29
3.1.3 የመምህራን አመራረጥ 30
3.1.4 የሴክሽንና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ 30
3.2 የጥናቱ መረጃ መሠብሠቢያ መሳሪያዎች 31
3.2.1 ምልከታ 31
3.2.2 የፀሁፍ መጠይቅ 32
3.2.3 ቃለ መጠይቅ 32
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ 33
ምዕራፍ አራት የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት 34
4.1 የተጠኚ መምህራን መግለጫና የትምህርት ቤቶች አደረጃጀት 34
4.2 የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያለው እገዛ 35
4.2.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና 35
4.2.2 ከመምህራን የቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ 37

4.3 የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን
ለማከናወንና የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያለው አስተዋጸ 38
4.3.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና 38
4.3.2 ከተማሪዎቹ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና 41
4.3.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ 442
4.4 የክፍለ ጊዜው ተግባራት (ክንውኖች) የማዳመጥና የመናገር
ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና 43
4.4.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና 43
4.4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የመረጃ ትንተና 44
4.5 መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት
የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችና ስልቶች.....45
4.5.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና 46
4.5.2 ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና 49
4.5.3 ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘ ምላሽ.....52
4.6 መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉት
ጥረት 54
4.6.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና.....54
4.6.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና 57
4.6.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ 58
4.7 መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው
ግንዛቤ.....60

4.8 የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የመምህሩ
መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ ያላቸው እገዛ 61

ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ 63

5.1. ማጠቃለያ 63

5.2. የመፍትሔ ሀሳብ 65

ዋቢ መፅሀፎች 67

አባሪ አንድ 71

አባሪ ሁለት 74

አባሪ ሶስት 78

የሰንጠረዥ ማውጫ

ገጽ

ሠንጠረዥ አንድ፡- የተጠኚ መምህራንና የትምህርት ቤቶች መግለጫን
የሚያሳይ 33

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን
ለማቀናጀትና ለማዳበር ያለው እገዛ ምን እንደሚመስል ለማወቅ
ከምልከታ የተገኘ ምላሽ 35

ሠንጠረዥ ሶስት፡- የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂል
ደረጃዎችን ለማከናወንና የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት
ያላው ሚናምን እንደሚመስ ለመፈተሽ በተደረገው
ምልከታ የተገኘው ምላሽ 38

ሠንጠረዥ አራት፡- የክፍለ ጊዜዎቹ ይዘት የመማዳመጥና የመናገር
ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወንና የተማሪዎቹን ፍላጎት
ለመማነሳሳት ያለው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ
ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ 39

ሠንጠረዥ አምስት፡- የክፍለ ጊዜው ተግባራት (ክንውኖች) የማዳመጥና
የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ምን
እንደሚመስል ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ 41

ሰንጠረዥ ስድስት፡- የክፍለ ጊዜው ተግባራት (ክንውኖች) የማዳመጥና
የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ምን
እንደሚመስል ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ.....43

ሰንጠረዥ ሰባት፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ
ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ስልቶችና ብልሃቶች ምን
እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ 45
ሰንጠረዥ ስምንት፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት
የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶችና ስልቶ ምን እንደሚመስሉ
ከተማሪዎች
የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ.....47
ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት
የሚያደርጉ ጥረት ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ.....53
ሰንጠረዥ አስር፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት
የሚያደርጉት ሚና ምን እንደሚመስል ከተማሪዎች የተገኘ ምላሽ 55

አጠቃለሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሠሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥ ክሒልን ከንግግር ክሂል ጋር ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚተገበር ቅንጅታዊ አቀራረብን ይጠቀማሉ? ከተጠቀሙ ደግሞ ከቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ አንጻር ምን እንደሚመስል በመፈተሸ፣ የታዩትን ደካማ ጎኖች የሚሻሻሉበትን መንገድ ማፈላለግና የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም ነው፡፡ ይህ ጥናትም በሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት የተካሄደ ነው፡፡

ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃል መጠይቅ አማካይነት የተገኙ ሲሆን በክፍል ውስጥ ምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች በሰንጠረዥ ተደራጅተው በቁጥርና በመቶኛ ተተንትነው እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡ በቃል መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በምልከታ ለተገኙ መረጃዎች አጋዥ ሆነው ቀርበዋል፡፡

በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት በተገኙ መረጃዎች ትንተና ውጤት መሰረትም መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎቹን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ፣ መምህራን ከተማሪዎች ችሎታ፣ ዳራና ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ ይዘቶችን እንደማያቀርቡ፣ መምህራን ከመማሪያ መጽሀፉ በተጨማሪ ለአላማው ተስማሚ የሆኑ አጋዥ መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙና ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥና መናገር እንዳለባቸው መመሪያ እንደማይሰጡ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማቅረብ የተለያዩ ስንቶችን እንደ ፕሮጀክት ስራ፣ ሚና ጨዋታ፣ የመረጃ ክፍተትን መሙላት፣ ተያያዥ ታሪኮችን መተረክ፣ ክርክር፣ ውይይትና ችግር ፈቺ ተግባራትን እንደማይጠቀሙ፣ የተማሪዎችን ውይይት እንደማይመሩና እንደማይቆጣጠሩ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መማሪያ መጽሀፉ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማቅረብ አመቺ እንዳልሆነና መምህራን ስለክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ አጫጭር ስልጠናዎችና ዎርክሾፖች አለመሰጠታቸው ተፅእኖ እንዳሳደሩባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ በመጨረሻም ጥናቱ ለችግሮቹ መፍትሄ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ ሃሳቦችን አቅርቧል፡፡

ምዕራፍ አንድ

መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በማዳበርና በማጎልበት በታላሚው ቋንቋ ጥሩ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ይህም ይሆን ዘንድ የተለያዩ ክንውኖችን መፈፀም አስፈላጊ ነው (Ur፣ 1996፣ 15)። ከነዚህም ክንዉኖች ውስጥ ምን እና እንዴት እናስተምር? የሚለው ጥያቄ ግንባር ቀደም ሲሆን ይህም ይዘት መረጣና የማስተማሪያ ስልት መወሰንን ይመለከታል። በተለይ ከይዘት መረጣ በኋላ የማስተማሪያ ዘዴን መወሰን በጣም አስፈላጊ ነው። የማስተማሪያ ዘዴዎች ተብለው ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ደግሞ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያግዘው ተግባቦታዊ አቀራረብ ነው (Littlewood፣ 1981፣93)።

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብን አስመልክተው Byrne (1981፣108) እና McDonough and Shaw (1992፣ 201) የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርስ ተያይዘው አንዱ ሲነሳ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ክሂሎች ተሳስረው የሚቀርቡበት የቋንቋ ክሔሎችን የማስተማሪያ ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ። እንዲሁም Cunningsworth (1984፣20) የክፍለ ጊዜው ትምህርት ማዳመጥ ቢሆንና ተግባቦታዊ የቋንቋ መስተጋብር (Interaction) እንዲኖር ከተፈለገ የመናገር ወይም የፅሀፈት ክሂልን መጠቀም ያስፈልጋል። ስለዚህ ተማሪዎች አንድን ነገር ካዳመጡ በኋላ ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲገልጹ በማድረግ፣ በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው ሀሳቡን እንዲወያዩና የተለያዩ ተግባራትን እንዲሚፈጽሙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የቋንቋ ክሂሎች ተቀናጅተው እንዲቀርቡ ማድረግ ይቻላል በማለት ይገልፃሉ።

Byrne (1981፣108) በገሀዱ አለም የቋንቋ ክሔሎች ተፈጥሯዊ የሆነ ቅንጅት ስላላቸው አንድ ክሂል ስንጠቀም ሌላው ክሂል ተከትሎ መምጣቱ የግድ ነው። ይህም በቋንቋ መማሪያ ክፍል መታየቱ አይቀርም። ሆኖም ግን በመማር ማስተማር ሒደት የሚፈለገው የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ድንገት የሚከሰተውን ውህደት ሳይሆን ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚቀርብ፤ ተማሪዎቹን በልምምድ ብቁ የቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል

ቅንጅት ነው። ስለዚህ ተፈጥሯዊ ውህደት ለቋንቋ ትምህርት የሚያበረክተው አስተዋጾ ከፍተኛ ቢሆንም በመማር ማስተማር ሂደት ግን ብቻውን ምሉዕ ነው ሊባል አይችልም በማለት ይገልጻሉ።

Celce-murcia and Olshtain (2000፣180)፣ Cunningsworth (1984፣45) እና ሌሎች በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ክሒሎችን ነጣጥሎ ከማስተማር ይልቅ በቅንጅት በማቅረብ የተማሪዎቹን ተግባቦታዊ ብቃት ማጎልበትና ከክፍል ውጭ የሚገኘውን የቋንቋ አጠቃቀም ማለማመድ ይቻላል። ይህም ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ የበለጠ እንዲካኑት ያግዛቸዋል በማለት ክሂሎች ተቀናጅተው መቅረብ እንዳለባቸውና ቢቀናጁ የሚያስገኙትን ጠቀሜታ ያስረዳሉ።

በታላሚው ቋንቋ የተማሪዎችን ተግባቦት ለማጎልበት፣ ተነሳሽነት ለመፍጠር፣ ወዘተ. ተፈጥሯዊ የቋንቋዎች ውህደት በቂ አይደለም። ምክንያቱም ተፈጥሯዊ የቋንቋ ክሂሎች ትስስር ታቅዶ የሚተገበር ባለመሆኑ ከየትኛው የቋንቋ ክሂል ወደ የትኛው መሸጋገር እንዳለበት እና የቱላይ መቆም እንዳለበት አያሳውቅም። ስለዚህ ትምህርቱን በተሳካ መልኩ ለመተግበር ከክሂሎች ተፈጥሯዊ ትስስር በተጨማሪ በእቅድ እና በአላማ የተመሰረተ የክሂሎች ቅንጅት ያስፈልጋል (Byrne፣ 1981፣108) ።

አራቱ የቋንቋ ክሂሎች መረጃ በመቀበልና መረጃ በማስተላለፍ በሁለት ይከፈላሉ። መረጃ መቀበያ ክሂሎች ማዳመጥና ማንበብ (receptive skills) ሲባሉ መናገርና መፃፍ ደግሞ መረጃ ማስተላለፊያ (Productive skills) ይባላሉ። በሌላ በኩል ማዳመጥና መናገር በቋንቋ ለመዳ ጊዜ በመጀመሪያ የሚገኙ ሲሆኑ ማንበብና መፃፍ ደግሞ በመደበኛው ትምህርት ሊገኙ የሚችሉ ናቸው። ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ማዳመጥና መናገር ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል (ማረው፣ 1998፣206)።

Celce-murcia (1991፣89) ማዳመጥና መናገር በተግባቦት ሂደት ውስጥ ከሌሎች ክሂሎች ጋር ሲታዩ ሰፊ ሽፋን ያላቸው ስለሆኑ በቋንቋ መማር ሂደት ላይ ትኩረት ተሠጥቷቸው ቢቀርቡ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ የበለጠ ማዳበር እንደሚቻል ይገልጻሉ። እንዲሁም Grant (1989) ማዳመጥና መናገር በተግባቦት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ አስተዋጾ ያላቸውና ለወደፊቱም ትኩረት ሊሰጥ የሚገባቸው እንደሆኑ ያስገነዝባሉ። ማረው (1998፣172) በበኩላቸው ማዳመጥና መናገር በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ ከሌሎች ክሂሎች

ይበልጥ በስፋት እንገለገልባቸዋለን፡፡ ይኸውም በአማካይ ከምናነበው አራት እጥፍ እና ከምንፅፈው ስምንት እጥፍ የበለጠ እንጠቀምባቸዋለን፡፡ ስለዚህ እነዚህ ክሂሎች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷቸው በቅንጅት ሊቀርቡ ይገባል በማለት ሀሳባቸውን ይሰንዝራሉ፡፡

ይህንንም ሀሳብ Ur (1996፤127) ሲያስረዱ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎች መሰረታዊና ተዛማጅ በሆኑ ሂደቶች የተያያዙና ለሌሎች ክሂሎች መዳበር ያላቸው አስተዋፆ ከፍተኛ በመሆናቸው በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተቀናጅተው ሊቀርቡ ይገባል በማለት ይገልፃሉ፡፡

McDonought and Shaw (1992፤202) እና Byrne (1981፤ 108) በክፍል ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችን ትኩረት በመስጠት አቀናጅቶ ማቅረብ ያለውን ጠቀሜታ እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፤

- ቋንቋውን ተፈጥሯዊ በሆነ መቼት ለመማር አጋጣሚን ይፈጥራል፡፡
- ተማሪዎች በጥንድና በቡድን ሆነው የተለያዩ ተግባራትን እንዲሰሩ ያበረታታል፡፡
- ከክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ተማሪዎች ትርጉም ያለው ስራና እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ያበረታታል፡፡
- ነባራዊነት ያለው ቋንቋን እንዲጠቀሙ ያግዛል፡፡
- ትምህርቱን ያፋጥናል፡፡
- በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የተማሪዎቹን ተነሳሽነትና ተሳትፎ ይጨምራል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከዚህም የተነሳ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ትኩረት ተሰጥቷቸው በቅንጅት መቅረብ አለመቅረባቸውን ማረጋገጥ፤ ከቀረቡ ደግሞ የአተገባበር ስልታቸውን መፈተሽ የዚህ ጥናት ትኩረት ነው፡፡ አጥኚው ይህን ጥናት እንዲያከናውን ያነሳሱት የተወሰኑ ምክንያቶች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

ከዚህ በፊት አጥኚው የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ከማስተማር ይልቅ በተናጠል የሚያስተምሩ መሆኑን መመልከቱ፤

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማዳመጥና የመናገር ክሂል ትምህርት አሰጣጥ ብዙ ጊዜ ችግር ያለበት እና መምህራን እነዚህን ክሂሎች ትኩረት በመስጠት እንደማያስተምሩ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች (ለምሳሌ ንጉሴ 1997፣ ቶማስ 2002፣ ውድ አዲስ 2001፣ መንግስቱ 1997) ያመለክታሉ። ስለዚህ አጥኚው ምናልባት እነዚህ ችግሮች ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር የተያያዙ ይሆኑ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ለመፈተሽ በማሰቡ።

አጥኝው በማስተማር ላይ በነበረበት ጊዜ አብዛኛዎቹ መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂል የሚመድቡት ጊዜ በጣም አነስተኛ ከመሆኑም ባሻገር እነዚህን ክሂሎች መምህራን አቅደውና አላማ ነድፈው ሳይሆን ተፈጥሯዊ በሆነ ውህደት እንደሚተገበሩ ባገኘው ልምድ በማወቁ ነው።

1.2 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥ ክሒልን ከንግግር ክሂል ጋር ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚተገበር ቅንጅታዊ አቀራረብን ይጠቀማሉ? ከተጠቀሙ ደግሞ ከቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ጋር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። ይህንን አጠቃላይ አላማ መሠረት በማድረግ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር አላማዎች ይኖሩታል፤

- የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን ለመተግበርና የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል?
- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ሲያስተምሩ መርጃ መሳሪያዎችን ይጠቀሙ ይሆን?
- የመምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ ትምህርት አቀራረባቸው ምን ይመስላል? ተግባራቸውንስ በአግባቡ እየተወጡ ይሆን?

- መምህራን ስለቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤና ዕውቀት ምን ይመስላል?
- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ስልቶችና ብልሀቶች ምን ይመስላሉ? የሚሉ ናቸው።

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ያስተምራሉ? ካስተማሩስ አቀራረባቸው ምን ይመስላል? የሚለውን በመፈተሽ ለመረዳት ተችሏል። ጥናቱም ከዚህ በታች ያሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል የሚል እምነት አለ።

- የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል ከተፈተሸ በኋላ እንዴት መቅረብ እንዳለበት ይጠቁማል።
- የማዳመጥና የመናገር ክሂል በቅንጅት ሲቀርቡ ሊያስገኙ የሚችሉትን ጠቀሜታ ይገልፃል።
- የረጅምና የአጭር ጊዜ የመምህራን ስልጠና የሚሠጡ የትምህርት ተቋማትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች ለቅንጅታዊ የክሂል ትምህርት አቀራረብን ትኩረት ሰጥተው እንዲያሰለጥኑ ያመለክታል።
- ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ያለውን ጠቀሜታ የአማርኛ የቋንቋ መማሪያ መሳሪያዎችን ለሚያዘጋጁ ተቋማትና ግለሰቦች ይጠቁማል።
- በዚህ ጥናት ዙሪያ ማጥናት ለሚፈልጉ ባለሙያዎች መነሻ በመሆን ያገለግላል።

1.4 የጥናቱ ገደብ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለተለያየ አለማ፣ ለተለያየ የትምህርት ደረጃ የሚሠጥ ትምህርት ነው። ይሁን እንጂ ይህ ጥናት በ2003 አ.ም በአማራ ክልል በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥን ክሂል ከንግግር ክሂል ጋር ሆን ተብሎና ታስቦበት የሚቀርብ

ቅንጅታዊ አቀራረብን ይተገብራሉ? ከተገበሩ አተገባበሩ ምን እንደሚመስል በመፈተሽና የመፍትሔ ሃሳቦችን በማመላከት ላይ ብቻ የሚወሰን ነው። ጥናቱ በጊዜ፣ በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት በሶስት ትምህርት ቤቶች እና በአምስት መምህራን ላይ ብቻ እንደያተኩር ተደርጓል። በመሆኑም ጥናቱ በቀጥታ የሚመለከታቸው መምህራንን ሲሆን የግል ትምህርት ቤቶችና የተለያዩ የክፍል ደረጃዎች አልተካተቱም። ምክንያቱም አጥኚው ካለው የጊዜና የገንዘብ አቅም አንጻር አስቸጋሪ ስለሆነ ነው። እንዲሁም ሌሎች ክሊሎች፣ የእውቀት ዘርፎችና መማሪያ መፅሀፉ የዚህ ጥናት የትኩረት ነጥብ አይደሉም።

ምዕራፍ ሁለት

የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት

2.1 የማዳመጥና የመናገር ክሂል ምንነት

የማዳመጥና የንግግር ክሂል ከአራቱ ዋና ዋና ክሂሎች ውስጥ የሚገኙ ቢሆኑም ጥቅማቸው በሚገባ ታውቆ ስላልነበር በቋንቋ ትምህርት ዘርፍ ለረጅም አመታት ትኩረት ሳይሰጣቸው ቆይቷል። ይሁን እንጂ Maley and Sandra (1981፣4) እንደሚሉት በተለይ ከ1969 እ.ኤ.አ ወዲህ በቋንቋ መማር፣ በስነልሳን ሐሳቦች፣ በማስተማሪያ ስነ ዘዴዎችና ሞዴሎች ላይ አይነተኛ ለውጥ በመደረጉ የክሂሎቹ አስፈላጊነት እየጨመረ እንደመጣ ይጠቅሳሉ። ስለዚህ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ምንነትና በቅንጅት ቢቀርቡ ሊያስገኙ የሚችሉትን ጠቀሜታዎች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

2.1.1 የማዳመጥ ምንነት

በማዳመጥ ክሂል ምንነት ዙሪያ ብዙ ምሁራን የተለያዩ ብያኔዎችን ሠጥተዋል። ከነዚህም ምሁራን ውስጥ Underwood (1989፣1) ማዳመጥ በንግግር የተላለፈውን ሀሳብ ትርጉም አዘል በሆነ ሁኔታ ሀሳብን የማወቅ ወይም የመረዳት ሂደት ነው ሲሉ ይገልፃሉ። እንዲሁም Grant (1989) ማዳመጥ ከአንድ ንጥል ድምፅ ጀምሮ ውስብስብ መልእክት እስከ መረዳት ድረስ ያለውን ሂደት ያጠቃልላል። በመሆኑም ማዳመጥ በንግግር ሂደት ውስጥ ሰፊ ድርሻ ያለውና በአላማ የሚከናወን ተግባር ከመሆኑም ባሻገር በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ውስጥ በየጊዜው አገልግሎት ሊሠጥ የሚችል ክሂል ነው በማለት ያስረዳሉ።

ማዳመጥ ለሚደመጠው ነገር ትኩረት በመስጠት አውዳዊ ፍቺውን ለማግኘት ሲባል የሚከናወን ተግባር ነው። እንዲሁም ተናጋሪዎች የተወሰኑ ቃላትን በተወሰኑ አገባቦችና አጋጣሚዎች ሲጠቀሙባቸው ምን ማለታቸው እንደሆነ መለየት መቻልም ነው (Anderson and lynch፣ 1988፣1)።

ከላይ የቀረቡት ብያኔዎች እንደሚያስረዱት ማዳመጥ አንድ ሰው የተናገረውን ወይም የተነበበውን ጽሁፍ አዳምጧል ለማለት ከሚደመጠው ንግግር ውስጥ ፍሬ ሃሳቡን መለየት፣

ሃሳቡን በቀላሉ መረዳት፣ እንዲሁም የተረዳውን ነገር ለሌሎች ማስተላለፍና መተርጎም ሲችል ነው።

ማዳመጥ በተግባቦት ሂደት ውስጥ ከሌሎች ክሂሎች አንጻር ሲታይ ሰፊ ሽፋን ያለው ነው። ስለሆነም ማዳመጥ በተግባቦት ሂደት ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ Celce-muricia (1991፣89) ይገለጻሉ። እንዲሁም Underwood (1989፣7) የማዳመጥ ትምህርት በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን፣ እራስን ለማስተዋወቅ፣ መረጃ ለመለዋወጥ፣ ስሜትን ለመጋራትና ራስን ለማዝናናት ጠቀሜታ እንዳለውና ክሂሉም በትምህርት መዳበር እንዳለበት ይገልጻሉ። ማረው (1998፣172) ማዳመጥ በእለት ተእለት ህይወታችን ውስጥ ከማንኛውም የቋንቋ ክሂል ይበልጥ በስፋት ያገለግላል። ይሄውም በአማካይ ከምንናገረው ሁለት እጥፍ፣ ከምናነበው አራት እጥፍ፣ እንዲሁም ከምንጽፈው ስምንት እጥፍ የበለጠ እንደምናዳምጥ ያስረዳሉ።

በመሆኑም የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር የሚደመጥ ነገር ያስፈልጋል። የሚደመጠው ነገር ደግሞ በመቅረፀ ድምጽ (tape recorder) በማሰማት፣ የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችና ምንባቦችን በማንበብ ወዘተ... ሊሆን ይቻላል። ስለዚህ ለማዳመጥ ትምህርት የሚቀርቡት ይዘቶች ንዑሳን ክሂሎችን ለማስተማር አቅም ያላቸው፣ ከገሐዱ አለም የሐሳብ ልውውጥ ጋር በአቀራረብ የሚመሳሰሉ፣ አጭርና ግልጽ የሆኑ እንዲሁም የዲስኩር ባሕርያትን ያካተቱ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ገጠመኝና የክፍል ደረጃን ያገናዘቡ፣ ለውይይት የሚጋብዙና የሐሳብ ፍሰታቸው የተስተካከለ፣ በሚገባ የተቀነባበሩና የመረጃ እጦት (የሃሳብ ጉድለት) የማይታይባቸው ሊሆኑ ይገባል

የማዳመጥ ክሂልን በክፍል ውስጥ ሲቀርብ ሶስት ደረጃዎችን ይከተላል (በድሉ፣ 1996፣ Underwood፣ 1989፣ Snow and Perkins፣ 1979፣ 1983 እና Rixon፣ 1986) ። እነዚህም ደረጃዎች

ቅድመ ማዳመጥ (pre Listening)፡- ይህ ደረጃ ተማሪዎች ከሚቀርበው ንግግር (ጽሁፍ) ጋር ትውውቅ የሚያደርጉበት ነው። እንዲሁም የተማሪዎቹን የቀድመ እውቀት ሊጠይቁ የሚችሉ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ስለሚደመጠው ነገር እንዲገምቱ የሚደረግበት ደረጃ ነው። Underwood (1989) እንደሚገልጹት በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን የተለያዩ ሐሳቦችን በማንሳት ተማሪዎች የመነቃቃት ስሜት እንዲፈጥሩ ማድረግ፤ ከትምህርት

ርእስ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቀደመ እውቀታቸውን መመዘን፤ ተማሪዎች በትምህርቱ ርእስ ዙሪያ ይነገራል ብለው የሚጠብቁትን ነገር በመጠየቅ እንዲገምቱ ማድረግ፤ ለትምህርቱ የቀረበውን ይዘት በተገቢው መልኩ እንዲረዱ የአዳዲስ ቃላት ፍቺን ለተማሪዎች ማሳወቅ፤ ከሚደመጠው የትምህርት ይዘት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መርጃ መሳሪያዎችን በማቅረብ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ፤ በማዳመጥ ጊዜ ሊሰሯቸው የሚችሉትን ጥያቄዎችንና በማዳመጥ ሂደት የሚከናወኑ ተግባራት እንዴት መሰራት እንዳለባቸው አጠር ያለ ማብራሪያ መስጠት ይኖርባቸዋል (Under wood፤ 1989)።

የማዳመጥ ጊዜ (While Listening) ፡- በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የሚደመጠውን ርእሰ ነገር በጥልቀት የሚያዳምጡበትና ተፈላጊ መረጃዎችን የሚሰበስቡበት ነው። በመሆኑም ተማሪዎች የሚደመጠውን ጽሁፍ ወይም ንግግር በተመስጦ በመከታተል እና ማስታወሻ በመያዝ ልምምዱን በተገቢው ሁኔታ እንዲያካሂዱ የሚደረግበት ደረጃ ነው። በዚህ የማዳመጥ ደረጃ መምህራን ተማሪዎች ስእሎችን በትክክለኛ ቅድመ ተከተላቸው እንዲያስቀምጡ፤ ያልተሟሉ መረጃዎችንና እቅዶችን እንዲያሟሉ፤ አንድን ጽሁፍ (ንግግር) እያዳመጡ እያሉ ቀጥሎ ምን ሊመጣ እንድሚችል እንዲገምቱ፤ የሚነገረውን ነገር በቅደም ተከተል ማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እንዲያሰፍሩ፤ አያያዥ ቃሎችን የተለያየ ትኩረት ሰጥተው እንዲያዳምጡ ማድረግ ይገባቸዋል። ምክንያቱም እንደነዚህ ያሉ ቃላት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሀሳቦች መካከል ያለውን የእርስ በእርስ ዝምድና ስለሚገልጹ ነው (በድሉ፤ 1996)።

ድህረ ማዳመጥ (Post Listening)፡- በድህረ ማዳመጥ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተማሪዎች ባዳመጡት ንግግር ወይም ጽሁፍ መሰረት በሐሳብ መስማማትና አለመስማማታቸው ወይም ያዳመጡትን ከግላዊ ገጠመኝ (አስተያየት) ጋር በማዋሀድ ሊመልሷቸው የሚችሉትን ጥያቄዎች እንደተማሪዎቹ ማንነት በመጠየቅ የማዳመጥ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ደረጃ ነው (Rixon፤ 1986፤72)። በሌላ በኩል Snow and Perkins (1979) እንደሚገልጹት ድህረ ማዳመጥ ተግባር ተማሪዎች የፈለጉትን ወይም የጠበቁትን መረጃ በትክክል ማግኘታቸውን ወይም አለማግኘታቸውን የሚያረጋግጡበት፤ የይዘቱን ርእስ በጥልቀት ለመመርመርና የተናጋሪዎቹን ዝንባሌ ለማወቅ የሚሞክሩበት ደረጃ ነው። ከዚህም በተጨማሪ መምህሩ ምጋቢ ምላሽ (Feed Back) በቃል መስጠት፤ ተማሪዎቹ በጥንድ፤ በቡድንና በጋራ በመሆን የተሰጡትን መልሶች እንዲያመሳክሩ ማድረግ፤ በንግግሩ

(በተደመጠው ጽሁፍ) ውስጥ ሊያከራክሩ የሚችሉ ነገሮችን በመምረጥ ተማሪዎቹ እንዲከራከሩ ማድረግ፤ ባዳመጡት ጽሁፍ ውስጥ የተሰማቸውን ነገር እንዲናገሩ ማድረግ፤ ወዘተ. በዚህ ደረጃ ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባሮች ናቸው (Snow and Perkins፣ 1979)።

2.1.2 የንግግር ክሂል ምንነት

የንግግር ክሂል በቋንቋ ድምፆች አማካይነት የሚተላለፍ ሲሆን በማህበራዊ ህይወት ውስጥም የጎላ ሚና ይጫወታል። እንዲሁም ንግግር ማለት ከአፍ እንደወጣ መናገር ሳይሆን ስሜት ያፈለቀውን፣ የተመለከተውን፣ በማዳመጥና በንባብ የተገኘውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሐሳብን ለሌላ ወገን ሥርአት ባለው መንገድ ማስተላለፍ መቻል ነው (Celce-muricia፣ 1991፣126)።

Byaget (1887፣5) ንግግር የሁለት ንዑሳን ክሂሎች ጥምረት ነው። እነዚህም ንዑሳን ክሂሎች የ‹‹ሞተር›› ገጽታ ክሂል (motor perspective skill) እና መስተጋብራዊ ክሂል (Interactive skill) ይባላሉ። የ‹‹ሞተር›› ገጽታ ክሂል አንድ ሰው በስሜት ህዋሳት አማካይነት የተገነዘበውን፣ ያስታወሰውን ትክክለኛ የቋንቋ ድምጽና መዋቅር ጠብቆ መልዕክት የማስተላለፍ ሂደትን ሲመለከት መስተጋብራዊ ክሂል ደግሞ ለመግባባት የምናደርገውን ንግግር የመወሰን ችሎታን ይመለከታል። ይህም ተናጋሪው ምን? እና እንዴት? መናገር እንዳለበት ይወስናል (Byaget፣ 1887፣5)።

የንግግር ክሂል ለብዙ ጊዜያት ትኩረት ሳይሰጠው እንደምልልስ ልምምድ ተደርጎ የቆየ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ ለማሳደግ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት በአለም አቀፋዊ ሁኔታዎች በመታወቁ ትኩረት እያገኘ መጥቷል (Dale, R and Wolf, J ፣1988)።

ንግግር ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት በጣም ወሳኝ ነው። ተማሪዎች ትክክለኛውን ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን በመከተል መግባባት እንዲችሉና ሀሳባቸውን እንዲገልፁ የታቀደ የንግግር ክሂል ትምህርት ያስፈልጋል በማለት የንግግር ክሂል የመግባባት ሂደትን የሚያቀላጥፍ እንደሆነ Celce-muricia (1991፣128) ይገልፃሉ።

የንግግር ክሂልን ማረው (1998፣139) ሲገልፁ

> *መናገር ክሂል የሁለት ችሎታዎች ጥምረት ውጤት እንደሆነም ይታመናል የማህበራዊና የስነልሳናዊ። ክሂሉን ለማዳበር የቋንቋውን መዋቅራዊ ክፍልና ማህበራዊ አጠቃቀም አጣምሮ መለማመድ ያስፈልጋል። ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት እንዳለው ሁሉ ማህበራዊ (አጠቃቀም) ስርአትም አለው። ማህበራዊ ስርአቱም በመዋቅራዊ ስርአቱ ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል። ስለዚህም ተማሪዎች ሁለቱንም ለይተው እዲያውቁ ያስፈልጋል። የቋንቋውን ስርአት ጠብቀው፣ የቋንቋው ተጠቃሚ እንደሚለውና እንደሚጠቀምት አድርገው ሀሳባቸውን መግለጽ ብሎም በሚገባ መግባባት እንዲችሉ ሁለቱን ለይተው መማር አለባቸው።*

የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በሶስት ደረጃዎች ይቀርባል (Dale, R and Wolf,J፣ 1988) ። እነዚህም ደረጃዎች፡-

ቅድመ ንግግር፡- በዚህ ደረጃ ንግግር የሚደረግበትን ርዕሰ ጉዳይ ወስኖ መምረጥ፣ ንግግር የሚደረግበትን አላማ ማወቅ፣ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ አድማጭን መወሰንና ዋና ዋና ነጥቦች የሚሰፍሩበት ነው።

የንግግር ተግባራት፡- ተማሪዎች በንግግር ሂደት እያሉ የንግግሩን ርዕስ ለአድማጭ የሚያስተዋውቁበት፣ አላማውን በአጭሩ የሚገልፁበት፣ ንግግሩን ሳቢ አድርገው የሚያቀርቡበት፣ በአድማጭ የሚጠየቁትን ጥያቄዎች ማስታወሻ የሚይዙበትና ለተጠየቁት ጥያቄዎች መልስ የሚሰጡበት ደረጃ ነው። መምህራን የተለያዩ ተግባራትን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ትምህርቱን ስኬታማ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ድህረ ንግግር፡- የተላለፈውን መልእክት አድማጮች ምን ያህል እንደተገነዘቡት የሚገመገምበት ሂደት ነው። እንዲሁም አድማጮች ያስተረዱት ነገር ካላቸው አንዳንድ ጥያቄዎችን የሚጠይቁበትና አስተያየት የሚሰጡበት ደረጃ ነው።

በአጠቃላይ የማዳመጥና የመናገር ክሂል በእለት ተእለት የህሳብ ልውውጥ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አላቸው። ስለዚህ የማዳመጥና የመናገር ክሂል በተግባቦት ሂደት ውስጥ ያላቸው ድርሻ በጣም ከፍተኛ እንደመሆኑ መጠን በቋንቋ ትምህርት ሂደትም ትኩረት

ተሠጥኟቸው ሊቀርቡ ይገባል። የተማሪዎች የተግባቦት ችሎታ ይዳብር ዘንድም ክሂሎቹን በተናጠል ከማስተማር ይልቅ የተለያዩ ተግባራትና ክንውኖችን በማቅረብ ተዋህደው ቢቀርቡ የትምህርቱ አላማ የበለጠ ግብ ሊመታ ይችላል።

2.2. የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነት

ቋንቋን የመማር ማስተማር ሂደት ሲታሰብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ስልቶች አብረው ይነሳሉ። ይህም እንደ ትምህርቱ አላማና ግብ እንዲሁም በዘመኑ እንደነበረው የቋንቋ ፍልስፍና መሰረት የተለያዩ ማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ምሁራን ሲነደፉ ይታያሉ።

ከነዚህም ውስጥ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያግዘው ተግባቦታዊ አቀራረብ የቋንቋ ትምህርት በሚፈልገው ሁኔታ ግብ እንዲመታ ያግዛሉ ተብለው ከሚጠቀሱት አቀራረቦች ውስጥ አንዱ ነው (Littlewood፣ 1981፣ 93)።

በቋንቋ ትምህርት ከሚቀረፁት አብይት አላማዎች አንዱ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማዳበርና ማጎልበት እንደመሆኑ መጠን በቅርብ አመታት ወዲህ በቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ ከፍተኛ ትኩረት እየተደረገ መጥቷል (Byrne፣ 1981፣107)።

የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትን አስመልክተው Byrne (1981፣108) የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርስ ተሳስረው፤ አንዱ ሲነሳ አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሌሎች ክሂሎችን በማስከተል ተዋህደው የሚቀርቡበት የቋንቋ ክሂሎችን የማስተማሪያ ሂደት ነው በማለት ይገልፃሉ። ከዚህ ምሁር ሀሳብ የምንረዳው የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማስተማር ማለት በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን በማጣመርና በማስተሳሰር አንዱ ሲነሳ ሌሎቹ አብረው እንዲመጡ የሚደረግበት ዘዴ መሆኑን ነው።

Rivers (1981፣297) ተማሪዎች አንዱን ክሂል በሚማሩበት ጊዜ ሌሎች ክሂሎችንም አብረው የሚያጎለብቱበት ዘዴ ነው። ለምሳሌ የፅሁፍ ክሂልን ማስተማር ከተፈለገ የተማሪዎቹ የማዳመጥና የማንበብ ክሂል ችሎታቸው መዳበር ይኖርበታል። ምክንያቱም ተማሪዎች ጥሩ የሆነ የመናገር፣ የማዳመጥና የማንበብ ችሎታ ካላቸው ጥሩ ፀሀፊ ስለሚሆኑ ሌሎች ክሂሎችንም አያይዞ ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

በሌላ በኩል Cunningsworth (1984፣20) ተግባቦታዊ የቋንቋ መስተጋብር (Interaction) እንዲኖር ከአንድ በላይ በሆኑ የቋንቋ ክሂሎች መጠቀም ይፈልጋል። ተማሪዎች አንድን ነገር ካዳመጡ በኋላ ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲገልጹ በማድረግ፣ በቡድን ወይም በጥንድ በመሆን ባዳመጡት ላይ እንዲወያዩ እና የተለያዩ ተግባራትን እንዲፈፅሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል በማለት ይገልፃሉ።

እውናዊውን የቋንቋ አጠቃቀም ስንመለከተው ንግግር በማዳመጥ፣ ፅሀፈት በንባብ ወዘተ. የሚታገዝ ነው። በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የቋንቋ ትምህርት አላማም ተማሪዎች የታለሚውን ቋንቋ አጠቃቀም በትክክለኛው መንገድ እንዲጠቀሙ ማስቻል በመሆኑ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ማቅረቡ ተግባቦታዊ ብቃትን የማጎልበት አስተዋፆው ከፍ ያለ ነው (Gilbert፣ 1982፣29)።

በመሠረቱ በአንድ መማሪያ ክፍል አንድን የቋንቋ ክሂል ነጥሎ ማቅረቡ አስቸጋሪ ነው። የንግግር ክሂልን ለማስተማር ሲታሰብ የማዳመጥ ክሂል አብሮ መምጣቱ አይቀርም። ይህም የመምህሩን ትዕዛዝ፣ ንግግር የሚያደርጉትን ይዘት፣ ሠዎችን በሚጠይቁበት ጊዜ ወዘተ... የማዳመጥ ሂደትን ያስከትላል። እንደዚህ አይነቱን ትስስር የቋንቋ ባህሪ የሚፈጥረው ቢሆንም በቋንቋ ትምህርት ብቻውን በቂ አይደለም። ይህን ሀሳብ በተመለከተ Atkins et al (1996፣225) እንደሚከተለው ያብራሩታል፤

> *በገሀዱ አለም ህይወት አንድን የቋንቋ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ነጥለን የምንጠቀምበት ጊዜ አልፎ አልፎ ነው፤ በውይይት ወይም በክርክር ጊዜ ንግግርን ብቻ እንጠቀም ብንል አይቻልም።... በማንኛውም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም የሚደመጥ (የመምህር ወይም የሌሎች ተማሪዎች ንግግር)፣ በመምህርና በተማሪ ወይም በተማሪና በተማሪ መካከል የሚደረግ ንግግር ወዘተ ... ይኖራል። ይህ ደግሞ ከክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ ሊከናወን የሚችል ተግባር ነው። ነገር ግን በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተፈጥሯዊ የሆነው ውህደት በእቅድና በአላማ ተዘጋጅቶ ሊቀርብ ይገባል።*

ከጥቅሱ የምንረዳው በገሀዱ አለም አዳምጠን የማንወያይበት፣ አንድን ነገር አዳምጠን ወይም አንብበን መልስ የማንሰጥበት ጊዜ በጣም አነስተኛ እንደሆነ ነው። ይህ ደግሞ አንዱ የቋንቋ ክሂል ተነጥሎ የሚቀርብበት አጋጣሚ አነስተኛ መሆኑንና የቋንቋ ክሂሎች

የተሳሰሩ መሆናቸውን የሚያሳየን ነው። ለምሳሌ፡- አንድ መምህር የማዳመጥ ክሂልን አስተምራለሁ ብሎ ቢያስብ ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ ያዳመጡትን ነገር መረዳታቸውን ይጠይቃቸዋል። ጥያቄውን ለመመለስ ደግሞ ይናገራሉ፤ ከተናገሩም የማዳመጥ ክሂልን ብቻ ተጠቀሙ ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ንግግርም አብሮ መጥቷልና። እዚህ ላይ መታየት ያለበት አንዱ ክሂል ሌላውን ክሂል ተከትሎ የሚመጣበት ተፈጥሯዊ ውህደት ቢኖረውም ትኩረት ተሠጥቶትና ታቅዶበት ሊቀርብ እንደሚገባ ነው።

ተፈጥሯዊ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅትን በተመለከተ Byren (1981፣108) የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ድንገት የሚፈጠረውን ቅንጅት ሳይሆን ሆን ተብሎና ታቅዶበት የሚቀርብ፣ ተማሪዎቹን በልምምድ ብቁና የቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያግዝ ሂደት ነው።

የክሂሎች ቅንጅታዊ አተገባበር ከክፍለ ጊዜው የትምህርት እቅድ ጋር በሚስማማ መልኩ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባውን ክሂል በዋናነት ትኩረት እንዲቸረው ለማድረግ ያስችላል። ለምሳሌ ተማሪዎች አንዱን ነገር ካዳመጡ በኋላ ለመናገር ቢነሳሱ ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ የተፈጠረ ነው በማለት ሙሉውን ክፍለ ጊዜ ንግግር እንዲያደርጉ ማድረግ አይቻልም። ምክንያቱም አላማና እቅድ እስካልተያዘለት ድረስ። ነገር ግን በእቅድ የሚመሠረት ቅንጅት ምን ያህል ጊዜ አዳምጠው በምን መልኩ የተረዱትን ይገልፃሉ? የትኛው ቀድሞ የትኛው ይከተል? በማለትና የተማሪዎቹን ችሎታና፣ ፍላጎት የሚወስን ስለሆነ ይህ አይነቱ አቀራረብ የተማሪዎቹን የቋንቋ ብቃት ለማዳበር ያለው ሚና ላቅ ያለ ነው።

Atkins et al (1996፣226) በበኩላቸው የቋንቋ ክሂሎች በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚሆኑበት ጊዜ አላማ በመንደፍ በቅንጅት ሊቀርቡ ይገባል። በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች ከክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ የተለያዩ ውይይቶችን፣ ገባኤዎችን፣ ክርክሮችን እንዲሁም ዘገባዎችን በማዳመጥ ወይም የተለያዩ መፅሀፍትን በማንበብ ማስታወሻዎችን እንዲይዙ፣ ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ የሚና ጨዋታ እንዲያከናውኑ ወዘተ. ማድረግ ያስፈልጋል። እንደዚህ ባለ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ ደግሞ ክሂሎቹ የበለጠ እንዲዋሀዱ ያስችላል በማለት ይገልፃሉ።

ከዚህ በላይ የቀረቡት ሀሳቦች እንደሚያስረዱት የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ በስርአት የታቀደ፣ በአንዱ ክሂል ልምምዳዊ ተግባር ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ

ክሂሎችን በማምጣት እርስ በርስ ተቀናጅተው ተግባር ላይ የሚውሉበት ሂደት መሆኑን ነው።

2.3 የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ አስፈላጊነት

Oxford (2001፣2) የቋንቋ ክሂሎች ተናጠላዊ አቀራረብ በጥንታዊ የቋንቋ ትምህርት ዘመን ይተገበር ስለነበር የተማሪዎቹን የተግባቦት ብቃት ከመገደብ በተጨማሪ አጠቃላይ በትምህርታቸው ስኬታማ እንዳይሆኑ ያደርግ እንደነበር ያስረዳሉ። ቋንቋን በተለያየ መልኩ ለመጠቀም ክሂሎችን በማዋሀድና በተለያዩ ክንውኖች አሳታፊ በሆነ ሁኔታ በማስተማር ከተፈለገው ግብ ሊያደርስ ይችላል (Ur፣ 1996፣151)።

ከነዚህ ምሁራን እንደምንረዳው በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች ጥሩ የቋንቋ ተጠቃሚና የተግባቦት ብቃታቸውን ለማዳበር ክሂሎችን በተናጠል ከማስተማር ይልቅ የተለያዩ ክንውኖችን በመጠቀም ክሂሎችን በቅንጅት ቢማሩ ውጤታማ ሊሆኑ መቻላቸውን ነው።

Cunningsworth (1984፣20) በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ተግባቦታዊ ብቃታቸው እንዲጎለብት ከአንድ በላይ የሆኑ የክሂሎች ክንውን እንደሚፈልግና ከክፍል ውጭ ሊያገኙት በሚችል መልኩ ሊቀርብላቸው ይገባል። ሀሳቡንም በምሳሌ አስደግፈው ሲያብራሩ፤ በሠዎች መካከል የሚደረግ ምልልስን በምሳሌነት ብንመለከት ማዳመጥና መናገር ተከታትለው ይመጣሉ፤ ስለዚህ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚቀርበው የክሂሎች ትምህርት ተማሪዎቹን በሚያሳትፍ መልኩ፣ የገሀዱን አለም ህይወት የቋንቋ አጠቃቀምን በሚያለማምድ ሁኔታ እንዲቀርብ የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች በቋንቋው የመግባባት ብቃታቸው ይበለፅጋል፤ ቋንቋውን ከክፍል ውስጥም ሆነ ውጭ እንዲገለገሉበት ሁኔታዎችን ያመቻቻል በማለት ያስረዳሉ።

የቋንቋ ክሂሎች ውህደታዊ አቀራረብ የተማሪዎቹን የተግባቦት ብቃትና ተነሳሽነት ከመፍጠር ባሻገር ለመምህራንም ቢሆን ምቹ የሆነ የስራ ቅድመ ተከተል ይፈጥርላቸዋል። በመሆኑም በእቅድ የተመሰረተ ቅንጅታዊ የቋንቋ ክሂሎች አቀራረብን በክፍል ውስጥ መጠቀም የሚከተሉት ጠቀሚታዎች እንደሚኖሩት Byren (1981፣108) ይገልጻሉ።

ትምህርቱን ያፋጥናል፡- በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ትምህርቱ የተሳካ ይሆን ዘንድ ከመምህሩ በበለጠ ተማሪዎች በትምህርቱ ንቁ ተሳታፊና ብዙ ነገሮችን እንዲሰሩ ይጠይቃል። የቋንቋ ክሂሎች በቅንጅት ማቅረብ ድግሞ ተማሪዎች ትርጉም አዘል እና አሳታፊ ተግባራትን እንዲለማመዱ በማድረግ ቋንቋውን በበለጠ ለማስተማር ያስችላል።

ቋንቋውን ተፈጥሯዊ በሆነ አውድ የመጠቀም አጋጣሚን ይፈጥራል፡- በእውኑ አለም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርስ የተሳሰሩ እንደመሆናቸው መጠን በመማሪያ ክፍል ውስጥም ክሂሎች ተቀናጅተው ቢቀርቡ ነባሪያዊነት ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ይለማመዳሉ።

McDonough and Shaw (1994፣206) **በቋንቋ ክፍል ውስጥ የቋንቋ ክሂሎች** በቅንጅት ሲቀርቡ ተማሪዎች በአውድ ተደግፈው የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ እገዛ ሊኖራቸው ይገባል። ለምሳሌ አውዱ በስልክ መነጋገር ቢሆን ተማሪዎቹ ስልኩን አንስተው ሲነጋገሩ፣ መልዕክቱን ሲቀበሉ የማዳመጥ ክሂልን ያዳብራሉ። እንዲሁም ማስታወሻ የያዙትን ለሚመለከተው ሠው ሲናገሩ የንግግር ችሎታቸውን ያበለፅጋሉ። ይህ ሂደት ደግሞ በአግባቡ ከተተገበረ በእውኑ አለም ያለውን የቋንቋ አጠቃቀም ይለማመዱታል::

Cunnigsworth (1984፣49) **በበኩላቸውም ተማሪዎች** በታላሚው ቋንቋ የሚግባቡበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የእውናዊው አለምን የቋንቋ አጠቃቀምና ሁኔታዊ ተግባቦትን መሠረት ያደረገ የቋንቋ ክሂሎች ትስስር ልምምድን ይፈልጋሉ። ለምሳሌ፡- በአንድ ንግግር መሀል በትክክለኛው ጊዜ የሚያጋጥምን መልስ የማጣት ችግርና ያልተጠበቀ ንግግር እንዴት እንደሚያጋጥም ተማሪዎች በተፈጠረላቸው አውድ እንዲመለከቱት ማድረግ ይቻላል። ስለዚህ በክፍል ውስጥ የሚካሄድ ተግባቦታዊ ክንዋኔዎች የእውናዊውን አለም የቋንቋ አጠቃቀም መቼትን ሊተኩልን ይችላሉ በማለት ይገልፃሉ።

ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ እንደምንረዳው ተማሪዎች ትርጉም አዘል በሆነ ክንውኖች ወይም ተግባራት ከተጠመዱ፣ ቋንቋውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን መግለጽና የሌሎች ሠዎችን ሃሳብ መገንዘብ ከቻሉ ከክፍል ውጭ ከሚገኘው መቼት ጋር ከሚመሳሰል ትርጉም አዘል ተራክቦ (Interaction) ጋር ሊተዋወቁ እንደሚችሉ ነው።

የተማሪዎች ፍላጎት እንዲነሳሳ ያደርጋል፡- የቋንቋ ትምህርት አላማ ግብ እንዲመታ የተማሪዎች ተነሳሽነት (Motivation) ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ምክንያቱም ተነሳሽነት መማር ማስተማርን ስኬታማ ያደርጋል። ስለዚህ ተማሪዎች በመጀመሪያ ለመማር

መነሳሳት ይኖርባቸዋል። McDonough and Shaw (1994፣214) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች ከፍላጎታቸው ጋር የሚስማማ ነገር ቢቀርብላቸው በእጅጉ ይነሳሳሉ። ቅንጅታዊ የቋንቋ ክሂሎች አቀራረብ ደግሞ የቋንቋ ትምህርትን ሳቢ እንዲሆን ያደርጋል ሲሉ ይገልፃሉ። እንዲሁም Atkins et al (1996፣225) ቅንጅታዊ የቋንቋ ትምህርት ተግባራዊ የሆኑ ግንኙነቶች ስለሚኖሩት የመማር ፍላጎትን ይጨምራሉ በማለት የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ።

የተማሪዎቹን ተግባቦታዊና ግንዛቤያዊ ብቃታቸውን ያሳድጋል፡- የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት ማስተማር የተማሪዎቹን ተግባቦታዊና ግንዛቤያዊ ብቃታቸውን ማሳደግ ያስችላል። በቋንቋ ትምህርት የሚቀርበው ትምህርት ተማሪዎች እንዲናገሩ ወይም እንዲያዳምጡ ወዘተ. ብቻ ሳይሆን ቋንቋውን የማገናዘብ ችሎታቸውን እንዲያበለፅጉም ነው።

ተማሪዎች አንድን ንግግር ወይም የሚነበብላቸውን ፅሁፍ አዳምጠው ስለፅሁፉ መልዕክት እንዲናገሩ፣ በቡድን ወይም በጥንድ እንዲወያዩ፣ ተጨማሪ ሀሳቦችን ከተለያዩ ሠዎች በመጠየቅ አሠባስበው እንዲመጡና ያሰባሰቡትን ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እንዲወያዩ በማድረግ የተማሪዎቹን ተግባቦታዊና ግንዛቤያዊ ብቃታቸውን ማዳበር ይቻላል። ከተለያዩ ሠዎች ጋር የሚደረገውን ተግባቦት ይገነዘባሉ፣ የማሰብ፣ የማሰላሰል ችሎታቸውን ያበለጽጋሉ፤ ሀሳቡን የማደራጀት ብቃታቸውን፣ በአካላዊ እንቅስቃሴ ታግዞ የሚደረገውን ተግባቦት ወዘተ. ያሳድጋሉ (Littlewood፣ 1981፣84)።

በአጠቃላይ Byren (1986፣130) እና McDonough and Shaw (1994፣117) የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ በሁሉም ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ያግዛል፤ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ትርጉም አዘል ያለው ስራና ልምምድ እንዲያከናውኑ ያስችላል፤ አውድን በመፍጠር ተማሪዎችን ለማስተማር ያግዛል፤ ታላሚውን ቋንቋ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ የመጠቀም ሁኔታን ይፈጥራል፤ በጥንድና በቡድን በሚሠሩ መልመጃዎች ውስጥ ሁሉም ተማሪዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ እድል ይሠጣል፤ ተማሪዎች ከአንድ ክሂል በላይ በሆነ ተግባር ላይ በማሳተፍ በበለጠ ታላሚውን ቋንቋ እንዲማሩ ያስችላል፤ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን ስራዎች ላይ ክሂሎችን እንዲዳስሱ ያደርጋል፤ ተማሪዎች በተግባቦት ብቃታቸው ብቁ እንዲሆኑ ያስችላል በማለት በቋንቋ ትምህርት ላይ ያለውን ጠቀሜታ ያስረዳሉ።

2.4 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ የማቅረቢያ ዘዴዎች

የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ በማቅረብ በእውኑ አለም የቋንቋ አጠቃቀምን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው። በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ትክክለኛና ነባራዊነት ያለው የቋንቋ አጠቃቀምን ተግባራዊ በማድረግ ክሂሎችን አዋህዶ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተለያዩ ዘዴዎች አሉ።

Oxford (2001፣3)፣ Celce-muricia (1991፣313)፣ Hill (1986፣8) የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ ስርአተ ትምህርትና መርሀ ትምህርት ቀራጮች፣ መፅሀፍ አዘጋጆችና መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም እንዳለባቸው ጠቅሰው በተለይ ይዘትን መሠረት ያደረገ፣ ተግባር ተኮር የሆነ፣ ወይም ሁሉንም ዘዴዎች ያዋሀደ ዘዴን ተጠቅመው ክሂሎችን በተቀናጀ መልኩ ማቅረብ እንደሚችሉ ይገልፃሉ።

2.4.1 ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ (Content based integrated skills instruction)

ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርትን ለማስተማር በዋናነት ይዘት ላይ ትኩረት ያደረገ ትምህርት የሚያቀርብ ዘዴ ነው። ተማሪዎቹም የትምህርቱን ይዘት እየተማሩ የቋንቋ ችሎታቸውን ያዳብራሉ። Celce-muricia (1991፣316) "ይዘት ተኮር ዘዴ ዋና ትኩረቱ በቋንቋ ቅርጽ ላይ ሳይሆን ተማሪዎች በእርሰ ጉዳዩ ላይ በመመርኮዝ ሃሳቡን እንዲረዱና እንዲያስተላልፉ የሚያደርግ አቀራረብ ነው" በማለት ይገልፃሉ። ይህ ደግሞ የሚያሳየን የተለያዩ ይዘቶችን በታላሚው ቋንቋ መማር መቻሉን ነው። የዘዴው ዋና አላማም ቋንቋን በይዘት ማስተማር ነው።

የቋንቋ ትምህርት ዋና ትኩረት የተደመጠው ወይም የተነበበውን መልዕክት በመረዳት ላይ መሆን አለበት። ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ጊዜ ይዘትን በማስተማር የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ ማጎልበት ይቻላል። ምክንያቱም የሚቀርቡትን ሀሳብ በታላሚው ቋንቋ መልዕክትን መረዳት ከተቻለ ቋንቋውን ማወቅ እንደሆነ ነው። ይህም ተማሪዎች ትርጉም ባለው ቋንቋ እንደሚጠቀሙበትና የቋንቋ ክሂሎችንም በተቀናጀ መልኩ እንደሚገለገሉባቸው ይረዳል (Krashen፣ 1981፣42)።

Celce-murcia (1991፣323) ተማሪዎች የቀረበላቸውን ይዘት ትክክለኛነትን እንዲጠይቁ፣ ምሳሌዎችን እንዲያቀርቡ፣ በራስ አባባል እንዲገልፁ፣ ጭብጥ ሀሳብን እንዲናገሩ በማድረግ፣ ዋና ዋና ሀሳቡን እንዲያጠቃልሉ፣ ማን? ምን? ለማን? ለምን? አለ እያሉ በመጠየቅ የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ ይቻላል በማለት ያስረዳሉ። እንዲሁም Atkins et al (1996፣223) የቋንቋ መምህር መሠረታዊ ተግባር ተማሪዎች ክሂሎችን አዋህደው እንዲጠቀሙና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ ብቻ ሳይሆን የሌሎች የትምህርት አይነቶችን ይዘትቶችን በጥልቀት እንዲገነዘቡ ማድረግም ነው ይላሉ።

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ይዘት ተኮር የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ የቋንቋ ችሎታ ከማዳበር በተጨማሪ ተማሪዎቹ የተለያዩ ይዘቶችን በጥልቀት እንዲመረምሩ፣ ቋንቋውም በተለያዩ ይዘቶች መመሪያነት እንዲጠቀሙ በማድረጉ ጥሩ ዘዴ መሆኑን ነው። እንዲሁም ይዘት ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ በአውድና በትክክለኛ ሁኔታ የተደገፈ በመሆኑ ተማሪዎች ቋንቋውን በቀላሉና ቶሎ እንዲለምዱ ያግዛቸዋል። ቋንቋውን በቀጥታ ሳይሆን የተለያዩ ይዘቶችን በማቅረብ ሳይሰለቹ እንዲለማመዱ የሚያግዝ ዘዴ መሆኑን ነው።

2.4.2 ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ (Task based integrated skills instrauction)

ተግባር ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ ተግባር ላይ እየተሳተፉ ቋንቋን ለመማር የሚያስችላቸው ዘዴ ነው። Oxford (2001) ተግባር ተኮር ቅንጅታዊ የክሂሎች አቀራረብ ተማሪዎች ተግባቦታዊ በሆነ የቋንቋ ክንውኖች የሚሳተፉበት፣ ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀምን የሚያስገኙ ተግባራትን የሚያከናውኑበት ዘዴ መሆኑን ያስረዳሉ። እንዲሁም McDonough and Shaw (1994፣218) ሲያስረዱ በቡድን ተግባሮች ተማሪዎች በተላማጪው ቋንቋ ሲጠቀሙ፣ በቢጤዎቻቸውና በመምህራቸው አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በተለይ በስርአት የተዋቀሩ ክንውኖች በተማሪዎች መካከል የበለጠ ተግባቦት እንዲኖር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ። ይህም ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን እያቀናጁ እንዲጠቀሙባቸው ያግዛል። ዘዴው የተማሪዎችን መስተጋብር ከፍ ለማድረግ በጥንድና በቡድን ሆኖ መስራት እንደዋነኛ ስልት ይጠቀማል።

Byren (1986፣130) በበኩላቸው የተቀናጁ የክሂሎች ክንውን ለልምምድ ብቻ ሳይሆን ተፈጥሯዊ በሆነ መልኩ የመጠቀም አጋጣሚ ይፈጥራሉ። የቡድንና የጥንድ ተግባራት

ደግሞ ሁሉንም ተማሪ የሚያሳትፍ የተለያዩ ክሂሎች እንዲኖሩ ያስችላሉ በማለት ከላይ የቀረበውን ሀሳብ ያጠናክራሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለው ተግባር ተኮር ዘዴ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን በተለያዩ ተግባራትና ክንውኖች እየተሳተፉ የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንዲጠቀሙባቸው የሚያደርግ ዘዴ ነው። ዘዴውን መጠቀምም ተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀምን እየተገነዘቡ ተግባቦትን የሚያዳብሩበት፣ መረዳትንና መስተጋብራዊ ተረክቦን የሚያጎለብቱበት ዘዴ መሆኑን ነው።

2.5 የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያግዙ ስልቶች

የቋንቋ ክሂሎች አቀናጅቶ ለማስተማር የሚያስችሉ የተለያዩ ስልቶች እንዳሉ በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልፃሉ። ክሂሎቹም ተዋህደው እንዲቀርቡ በማድረግ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ማዳበር የሚችልበትን መንገድ ማወቅ ያስፈልጋል። የቋንቋ ክሂሎቹ በሚቀናጁባቸው ስልቶችና ይዘቶች እንደየተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታና፣ የክፍል ደረጃ የሚለያይ ቢሆንም ከተማሪዎቹ ደረጃ ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ ስልቶችን እየተጠቀሙ ማቀናጀት ይቻላል።

Byren (1986፣133)፣ Celce-murcia (1991፣337)፣ McDonough and Shaw (1994፣215) እና አለም (1995፣26) የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማቅረብ የሚያግዙ ስልቶችን እንደሚከተለው ጠቅሰዋል።

1. **ሀሳብን በቃል ማቅረብ** (Oral presentation)፡- ተማሪዎች የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅና ማስታወሻ በመያዝ ምን እንዳዳመጡ ለክፍል ጓደኞቻቸው በቃል የሚያቀርቡበት ነው፤ ውይይቱ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ሌሎቹ ተማሪዎች እያዳመጡ አጫጭር ማስታወሻዎችን፣ ድጋፊ ሀሳቦችንና ጥያቄዎችን በመያዝ በመጨረሻ መወያየት፣ መጠየቅ ይችላሉ። ይህ ደግሞ ሀሳብን በቃል ማቅረብ የተማሪወቹን የመናገር ችሎታ ያዳብራል፤ ንግግሩን ለማቅረብና ለማጠናከር ሠዎች በመጠየቅ ሲያሰባስቡ የማዳመጥ ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ያስችላቸዋል።

አለም (1995፣26) ይህ አይነቱ ብልሀት ክሂሎችን ከማቀናጀት ባሻገር ተማሪዎቹን የመናገር፣ የመወያየት፣ ከቋንቋው ውጭ የሆኑ እውቀቶችን የመፈተሽ፣ ሀሳባቸውን በቃል

በሚያቀርቡበት ጊዜ በአካላዊ እንቅስቃሴና በፊት ገጽታ አስደግፈው ሊገልጹ ስለሚችሉ ሁለንተናዊ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀምን ያዳብራሉ በማለት ይገልጻሉ።

2. የ‹‹ፕሮጀክት›› ሥራ (Project work)፦ McDonough and Shaw (1994፣215) የ‹‹ፕሮጀክት›› ሥራ ተማሪዎች ከመምህራቸው ጋር ወይንም ብቻቸውን የተለያዩ መረጃዎችን ከጽሁፍም ሆነ ቃለ መጠይቅ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻቸው የሚገልፁበት መንገድ መሆኑን ያስረዳሉ። Celce-murcia፣ (1991፣337) የ‹‹ፕሮጀክት›› ስራን በሚመለከት አንድ ብያኔ ባያስቀምጡም፤ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ የተለያዩ መረጃዎችን በማሠባሠብ ዘገባ የሚያቀርቡበት ስልት እና ክሂሎችን በተቀናጀ መልኩ እንዲጠቀሙባቸው የሚያግዝ ዘዴ እንደሆነ ገልፀዋል። ለምሳሌ፦ ተማሪዎች የአንድን ማህበረሰብ የአመጋገብ ስርአት አካባቢንና ጤናን ከግምት በማስገባት ዘገባ እንዲያከናውኑ ማዘዝ እንደሚቻል ይገልፃሉ። ይህ አይነቱ ስራ ደግሞ ተማሪዎችን ሙሉ በሙሉ በማሳተፍ፣ ወደስራው እንዴት እንደሚሄዱ፣ ተተኳሪዎቹ ማን እንደሚሆኑ፣ እንዲነጋገሩ እንደሚያደርጋቸው ያብራራሉ።

3. ሚና ነጠቃ /ማስመሰል (role play/ simulation)፦ Byren (1981፣8) ማስመሰልና ሚና ነጠቃ ለቋንቋ ትምህርት በጣም አስፈላጊ መሆኑን ሲያብራሩ፤ ተማሪዎች ለመናገር የፈለጉትን እና እንዴት እንደሚሉት የሚወስኑት ራሳቸው ስለሚሆኑ ምርጫቸውን በመጠበቅ ፈጥረው እንዲናገሩ፣ ሀሳባቸውን በራሳቸው አገላለጽ እንዲያብራሩ፣ በተለያዩ መልኩ ቋንቋውን እንዲጠቀሙበት ያደርጋል፤ መምህራንም የተማሪዎች ችግር የት ላይ እንደሆነ እንዲለዩ ያስችላቸዋል በማለት ያስረዳሉ። እንዲሁም Mc Donough and shaw (1994፣217) ሚና ነጠቃ ወይም ማስመሰል ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል ዋናኛው መሆኑን ይገልፃሉ። ብልሀቱ አንድን ባህሪ (ነገርን) በመወከል በማስመሰል ወይም በመወከል በክፍል ውስጥ ክሂሎችን አዋህደው እንዲጠቀሙባቸው ከማስቻሉም በላይ ተማሪዎች ስሜታቸውን በመግለጥና በመዝናናት እንዲለማመዱ ያደርጋቸዋል ሲሉ ያብራራሉ።

4. ውይይት፦ ተማሪዎች አንድ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ፣ ሃሳብን በጋራ እንዲካፈሉ፣ በቡድናቸው መፍትሄ እንዲፈልጉ፣ ወዘተ. ሊወያዩ ይችላሉ። ከውይይቱ በፊት አላማው በመምህሩ ሊገለጽ ይገባል። ይህም በመሆኑ ተማሪዎች በሌላ ጨዋታ ጊዜያቸውን እንዳያባክኑና ወደ ነጥቡ እንዲያተኩሩ ይረዳቸዋል።

5. የመረጃ ክፍተትን መመላት፡- ይህ የተግባር አይነት ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው። ብልሃቱም አንድ ተማሪ ለሌላው መረጃ በመስጠት በጥንድ (በቡድን) የሚሰራ ነው። ችግሮችን ለመፍታትና መረጃን ለማሰባሰብ ስለሚጠቅም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በንቃት እንዲሳተፉ ይረዳል።

6. ታሪክ ነገራ፡- ተማሪዎች ቀደም ሲል የሰሙትን ታሪክ ወይም በራሳቸው የፈጠሩትን ሃሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ የሚያግዝ ስልት ነው። ስልቱም የተማሪዎችን ሃሳብ የመፍጠር ችሎታን ያዳብራል። እንዲሁም ተማሪዎች ሃሳባቸውን መግቢያ፣ ሃተታና ማጠቃለያ ወይም መደምደሚያ በያዘ ቅርጽ ማቅረብ እንዲለማመዱ፣ የታሪኩን ባህሪያትና መቸት አስመስለው እንዲያቀርቡ ይረዳል።

7. ቃለ መጠይቅ፡- ይህ የማስተማሪያ ብልሃት ተማሪዎች የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን ለመረዳት ሰዎችን ቃለ መጠይቅ የሚያደርጉበት ነው። መምህሩ ምን አይነት ጥያቄ እንደሚጠይቁ፣ እንዴት እንደሚጠይቁና ለመጠየቅ መከተል ያለባቸውን መንገድ ሊገልጽላቸው (መመሪያ ሊሰጣቸው) ይገባል። ብልሃቱም በክፍል ውስጥ ብቻ ሳይሆን ከክፍል ውጪም ተማሪዎች ልምምድ እንዲያደርጉ ይጋብዛል።

ከላይ ከተጠቀሡት ብልሀቶች በተጨማሪ አለም (1995፣26)፣ Byren (1981፣15) McDonough and Shaw (1994፣14) ድራማዎች በመስራት፣ ‹‹ጌሞችን›› በመጫዎት፣ እይታዊና ድምፃዊ መሳሪያዎችን በመጠቀም ወዘተ. እንዲያዳምጡ፣ ማስታወሻ እንዲይዙ፣ በአንድ ርዕሰ ነገር ዙሪያ ንግግሮችን እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸትም የተቀናጀ ክሂልን ለማዳበር የሚረዱ ብልሀቶች መሆናቸውን ይገልጻሉ።

2.6 የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት የመምህሩ ሚናና ተግባር

የቋንቋ ክሂሎች ተቀናጅተው እንዲቀርቡ ለማድረግ የመምህራን ሚና ወሳኝ ነው። መምህራን የክፍሉን ሁኔታ በመቆጣጠር ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት ከፈጠሩ ተማሪዎች ቋንቋውን በብቁ ሁኔታ ለተግባቦት አላማ ይገለገሉበታል። ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ ተግባራት የሚሳተፉ ከሆነም ተፈጥሯዊ የቋንቋ አጠቃቀምን ይለማመዳሉ። በዚህም የቋንቋ ክሂሎች ተቀናጅተው ይቀርባሉ። ይህን ሀሳብም Atkins et al. (1996፣227) የቋንቋ መምህራን ገለጻና ማብራሪያ ለተማሪዎች በመስጠት የማዳመጥና ጥሩ ማስታወሻ የመውሰድ ችሎታን የሚዳብሩበትን ተግባራትና ልምምድ ማቅረብ አለባቸው

በማለት ያስረዳሉ። እንዲሁም መምህራን ተማሪዎች ማስታወሻቸውን እንዲያጠናክሩና የመረዳት ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዲወያዩ ማድረግ ይገባቸዋል። ይህ ደግሞ ተማሪዎች የመናገር አጋጣሚን ስለሚፈጥርላቸው የተግባቦት ብቃታቸውን ለማዳበር የሚስችል ዘዴ መሆኑን ይገልፃሉ (Atkins et al.፣ 1996፣227)።

Dale, R and Wolf, J (1988) ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ተግባቦትን እንዲፈጥሩ በጥንቃቄ የተዘጋጀ ትምህርት፣ የክፍል ልምምድና ክንውን ይሻሉ። ስለዚህ መምህራን የቋንቋ ክሂሎች በስርአት ተሳስረው እንዲመጡ ማድረግ እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ። ሀሳቡንም McDonough and Shaw (1994፣202) ሲያጠናክሩ መምህራን የቋንቋ ትምህርትን የሚያከናውኑት ተማሪዎች ጥሩ ተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማድረግ ስለሆነ ተማሪዎች ክሂሎችን እያቀናጁ ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ተግባራት መስጠት እንደሚኖርባቸው ይገልፃሉ።

ከላይ የቀረቡት ሀሳብ መምህራን የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ይጎለብት ዘንድ የተለያዩ ተግባራትን ክንውኖችን በጥንቃቄ በማዘጋጀትና ተማሪዎች ክንውኖችን በቡድን ሆነ በጥንድ በሚተገብሩበት ጊዜ ምን ዘዴና እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው መከታተል፣ ማመላከት እንዳለባቸው ያስረዳሉ።

Gower et al. (1995፣154) ተማሪዎች የተግባቦት ሐሳቦችን እዲለማመዱ በክፍል ውስጥ መስተጋብር (Interaction) ይፈልጋሉ። በዚህ ጊዜ የመምህራን ሚናም የቡድንና የጥንድ ስራዎችን መስጠት፣ ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲወያዩ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ፣ መገምገምና መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። በሌላ በኩልም ምቹ የሆኑ የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርባቸዋል። መምህራንም ይህን ተግባራዊ በማድረግ የክሂሎችን ትምህርት እውናዊ በሆኑ ተግባራት አዋህደው በማቅረብ ተናጠላዊ የክሂሎች ትምህርትን ማስወገድ ይኖርባቸዋል።

Dale, R and Wolf, J (1988) የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብን ተግባራዊ ለማድረግ መምህራን ከክፍል ተግባራት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የተለያዩ መጽሀፎችና ታሪኮች ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ ማንበብ፣ የክፍል ውይይት ማስደረግ፣ ንግግርን መምራት፣ የተለያዩ ቡድኖችን በመመስረት ማሳተፍ፣ ተማሪዎች የተለያዩ አስተያየቶችን እንዲሰጡ፣ እንዲጽፉ፣ እንዲናገሩ ወዘተ. በማድረግ መተግበር ይኖርባቸዋል። እነዚህንም ተግባራት

በተገቢው እንዲከናወኑ መምህራን የቋንቋ ክሂሎች በምን መልኩ መቀናጀት እንዳለባቸው ማወቅ ይጠበቅባቸዋል በማለት ያስረዳሉ።

እንዲሁም Oxford (2001) መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው ለማቅረብ የሚከተሉትን ሀሳቦች ማጤን እንዳለባቸው ይገልጻሉ።

- ክሂሎችን ለማቀናጀት የሚያግዙ የተለያዩ መሣሪያዎች እና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን መምረጥ
- የቋንቋ ክሂሎች ተቀናጅተው በሚቀርቡባቸው የተለያዩ መንገዶች ማስተማር
- እየተጠቀሙበት ያለው የአቀራረብ ዘዴ ክሂሎቹ ምን ያህል እንደተቀናጁ መገምገም።
- መምህራንም ከነዚህ በመነሳት በስርአት ማቀድ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችና ብልሀቶችን መጠቀም ይኖርባቸዋል። እንዲሁም ተማሪዎቹ ተፈጥሯዊ የቋንቋ አጠቃቀምን እንዲያዳብሩ፣ ትምህርቱ እውናዊ እንዲሆንና በቋንቋው ጥሩ ተግባቦት እንዲኖራቸው በተለያዩ ተግባራት አማካይነት ክሂሎችን በማቀናጀት ማከናወን ይኖርባቸዋል።

Harmer (1991፣235-243) እና Richards and Rodgers (1986፣32) የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት ለማቅረብ መምህራን የሚከተሉትን ነገሮች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባሉ።

ትምህርቱን መቆጣጠርና መምራት፣ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባር በሚተገብሩበት ጊዜ ተገቢውን ቋንቋ በተገቢው ሁኔታ መጠቀማቸውን ትኩረት ሰጥቶ መከታተል፣ ሁሉም ተማሪዎች በተግባሩ ላይ እኩል መሳተፋቸውን ማረጋገጥና ተግባራትን በመምረጥ ማመቻቸት፤ ተማሪዎቹን ማነሳሳትና ማስታወስ፤ ተሳታፊና ምንጭ (source) መሆን፤ አጠናካሪና ተመራማሪ መሆን ይኖርባቸዋል።

በአጠቃላይ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ትምህርቱ የተሳካ እንዲሆን የመምህራን ያልተቆጠበ ጥረት ያስፈልጋል። ስለዚህ መምህሩ የተማሪዎቹን ጠባይ፣ ችሎታና እድሜ የሚያውቅ፤ ለፈጠራ ስራ ዝንባሌ ያለው፤ ተማሪዎቹን በሚገባ መገምገም

የሚችል፤ የማስተማር ፍላጎት ያለውና ከተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር የሚችል መሆን ይኖርበታል።

2.7 የቋንቋ መማሪያና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ለክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው አስተዋፆ

2.7.1 መርሀ ትምህርት

መርሃ ትምህርት ከስርአተ ትምህርት ጠበብ ያለ፤ የትምህርት ይዘቶችን ለማዋቀር በመነሻነት የሚያግዝ፣ የትምህርቱ አጠቃላይ ዝርዝር አላማዎች በመግለፅ የሚያሳይ፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን የሚጠቁም፣ ትምህርቱ የሚቀርብበትን የጊዜ ገደብ የሚያመለክት፣ የምዘና ዘዴዎችንና መርጃ መሳሪያዎችን የሚጠቁም ንድፍ ወይም ሰነድ ነው (Cunningsworth፣ 1984፣22)።

Ellis (1984፣202) የቋንቋ መርሃ ትምህርት ተማሪዎች ሊያከናውኗቸው የሚገቡ ተግባቦታዊ ተግባራትን መዘርዘርና ተለጣጥቀው (Sequentially) እንዲቀርቡ ማድረግ የሚያስችል መሆን አለበት ሲሉ ይገልፃሉ። እንዲሁም Widdowson (1990፣129) የቋንቋ መርሀ ትምህርት ለመምህራን እንደመመሪያ ሆኖ እንደሚያገለግላቸው፣ የተለያዩ ስነ ዘዴዎችን በማሳየት የመማር ማስተማር ሂደትን እንዴት እንደሚተገብሩና የመማር ክንውኖችን እንዲያጎለብቱ የሚያሳይ መሆኑን ይገልጻል። ይህም ለመምህራን እንደ አንድ አጋዥ የትምህርት መሳሪያ ሆኖ እንደሚያገለግል ይጠቁማሉ።

2.7.2 የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሀፍ

የመምህሩ መምሪያ የተማሪውን የመማሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊያስተምር እንደሚችል አቅጣጫ ቋሚ መሳርያ ሲሆን የተማሪው መጽሀፍ ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲሠሩበት፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዲከታተሉበት የሚያስችል የማስተማሪያ መሳርያ ነው። Harmer (1991፣257) እና Richard and Rodgers (1986፣25) በበኩላቸው የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፎች የመማር ማስተማር ሂደትን የሚመሩ፣ የትምህርቱን መነሻና መድረሻ የሚጠቁሙ፣ የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፈው የሚያቀርቡ፣ መልመጃዎችና የተለያዩ ተግባራት በማቅረብ ተማሪዎች

እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ። በሚዘጋጁበትም ጊዜ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው እንደሚገባ አክለውም ይጠቅሳሉ።

Byren (1981፣109) ጠቅለል ባለ መልኩ በማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚቀርቡ የቋንቋ ተግባራት ከሌሎች ተግባራት ጋር የሚያያዙበት ሁኔታን መፍጠር የሚችሉና ተማሪዎች በቀረቡት ይዘቶች ላይ ክሂሎችን አዋህደው ሀሳባቸው እንዲገለፅ የሚስችል መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ። አንድ ተግባር ሌላውን እያስከተለ በሚቀርብበት ሂደትም መምህራን ከየት ወዴት እንደሚቀጥሉ የማሳየት የተመቻቸ የአሰራር ሂደት ሊፈጥርላቸው እንደሚገባ አያይዘው ይገልጻሉ።

2.8 የቀደምት ስራዎች ቅኝት

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች እንደተከናወኑ ይታወቃል። ከእነዚህም ምርምር ከተደረገባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንደኛው የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዙሪያ የተካሄደ ጥናት ነው። የተሻለና ወቅቱን የጠበቀ የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ትምህርት ሊኖርም የሚችለው በተለያየ ጊዜያትና በየደረጃው ከሚካሄዱት ጥናቶች ሲኖሩ ነው። የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ዘዴ ተማሪዎች ጥሩ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ከማስቻሉም በላይ ቋንቋውን ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ እንዲገለገሉበት የሚያግዝ የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ነው። ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ በዚህ ርዕስ ዙሪያ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተካሄዱት ጥናቶች በጣም አነስተኛ ናቸው። ይህ ደግሞ በርዕሱ ዙሪያ በጣም ጠንካራና ብዙ ጥናቶች እንደሚያስፈልጉት ያመለክታል። ከዚህ በመቀጠል ከአሁን በፊት በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ዝምድና ለመቃኘት ተሞክሯል።

በየነ ማሞ (1985) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የቋንቋ ክሂሎችን የሚያዳብሩ ናቸው?" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነበር። የጥናቱ አላማ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመፃፍን ክሂል የሚያዳብሩ መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ሲሆን በ1984 ዓ.ም የተዘጋጀውን መማሪያ መፅሀፍ መሠረት በማድረግ በፍትነታዊ የምርምር ዘዴን (experimental research) መጠይቅ መረጃ በመሰብሰብ ጥናቱን አካሂዷል

አታኽልቲ መኮንን (1998) "የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቋንቋ ክሂሎችን ትኩረት ሰጥተው አቀናጅተው ያቀረባሉ?" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አቅርቦ ነበር። የጥናቱ አላማ በአዲስ አበባ መስተዳድር የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ላይ ለተግባራዊ ልምምድ ታስቦና ሆን ተብሎ የሚተገበረውን ልምምዳዊ የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብን (practical integration) መፈተሽ ሲሆን የገላጭ ምርምር ዘዴን በመከተል በምልከታ፣ ከመምህራን በቃለ መጠይቅና በፅሁፍ መጠይቅ አማካይነት መረጃ በመሰብሰብ ጥናቱን አካሂዷል። ጥናቱም ክሂሎቹን ለማቀናጀት የሚቀርቡ ይዘቶች ተማሪዎቹ እንዲያነቡ፣ እንዲያዳምጡ፣ እንዲፅፉ፣ እንዲናገሩና በቡድንም ሆነ በጥንድ እንዲወያዩ የሚያግዙ መሆናቸውን፣ መምህራን ስለ ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ጥሩ እንዲሆን፣ መምህራን በተማሪ መፅሀፍ የቀረቡትን መልመጃዎች ለመጨረስ እንደሚሯሯጡ፣ ከተማሪዎች የሚመጡትን መልሶች ወደ ተማሪዎች ከመመለስ ይልቅ መምህራን ራሳቸው ዘለግ ያለ ማብራሪያ እንደሚሰጡ፣ መምህራን በተለያዩ ስልቶች አማካይነት የቋንቋ ክሂሎችን ለማቀናጀት መሞከር ጊዜ ማጥፋት እንደሆነና ብዙ የተማሪ ቁጥር ባለበት ክፍል አስቸጋሪ ነው ብለው እንደሚያስቡና ክሂሎቹን ለማቀናጀት አጋዥ መሳሪያዎችን መምህራን እንደማይጠቀሙ አረጋግጧል።

Gizacew Alemu (2001) "exploration of the problem in teaching English language skills an integrated way" 'A case of Addis Ababa በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ነው። የጥናቱ አላማ ክሂሎች ተቀናጅተው በሚቀርቡበት ጊዜ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ምን እንደሆኑ በመመርመር የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ ሲሆን ጥናቱን በምልከታ፣ በመምህራን ቃለ መጠይቅና በጽሁፍ መጠይቅ አማካይነት መረጃዎችን በመሰብሰብ ጥናቱን አከናውኗል።

እንዲሁም Teferi Labisso "An exploration of Teacher practice in integrated language skills in the teaching of English to grade 12 selection school in wolayta" በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ሲሆን የጥናቱ አላማም የ12ኛ ክፍል መምህራን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅተው እንደሚያቀርቡ መመርመር ሲሆን መረጃውን በምልከታ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ አማካኝነት በመሰብሰብ ጥናቱን አከናውነዋል።

ከፍ ሲል ከተዳሰሱት ጥናቶች በሚያነሷቸው ርዕሰ ጉዳዮች ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰሉም ልዩነታቸው የጎላ ነው። የበየነ ማሞ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው የ9ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ላይ በመሥራቱ ሲሆን የሚለየውም በመማሪያ መጽሀፍ ላይ ትኩረት በማድረጉና ሁሉንም የቋንቋ ክሂል ላይ ከማተኮሩም ባሻገር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ክሂሎችን አቀናጅተው ያቀረቡ እንደሆነ የማይፈትሽ በመሆኑ ነው እንዲሁም አታኽልቲ መኮንን ከዚህ ጥናት ጋር ቢመሳሰልም አጠቃላይ የክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ በማተረኮሩ ከጥናቱ ጋር ይለያያል። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ጥናት ከአታኽልቲ መኮንን ጥናት ጋር በተተኳሪ ቦታና በጊዜ ይለያያሉ።

Gizacew እና Teferi በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተጠኑ በመሆናቸው፣ በክፍል ደረጃ ማለትም በ1ኛ ደረጃ ትምህርርት ቤት እና በ12 ክፍል ማተኮራቸው፣ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ላይ መሰራታቸው ከጥናቱ ጋር ይለያያሉ። በአጠቃላይ ይህ ጥናት ከላይ ከቀረቡት አራት ጥናቶች ጋር ትኩረት ባደረጉበት ክሂል፣ በቦታ፣ በጊዜ ይለያያሉ።

ምዕራፍ ሦስት

የጥናቱ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመረጃ ምንጮች አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አይነትና አደረጃጀት፣ የመረጃ አሰባሰብ ሂደቱና የጥናቱ አጠናን ስልት በዝርዝር ቀርበዋል። ጥናቱም የተከተለው አይነታዊ ምርምርን (qualitative research) ሲሆን አሀዛዊ ምርምር ዘዴን (quantitative research) ደግሞ በደጋፊነት ተጠቅሟል። አቀራረቡም ገለፃዊ ዘዴን (descriptive method) የተከተለ ነው።

3.1 የናሙና መረጣ

በዚህ ጥናት ውስጥ የክልል፣ የዞን፣ የትምህርት ቤት፣ የመምህራንና የተማሪዎች ናሙና መረጣ ተካሂዷል። የእያንዳንዱ የናሙና አመራረጥም ቀጥሎ ይቀርባል።

3.1.1 የክልልና የዞን አመራረጥ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የአማራ ክልል በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ሊመረጥ ችሏል። ምክንያቱም አጥኚው ከሌሎች ክልሎች በተሻለ መልኩ መረጃዎችን ማግኘት እንደሚችል ስለገመተ ነው። አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በስሩ አስራ አንድ ዞኖችን አካቶ ይዟል። እነዚህንም ዞኖች ጥናት ለማካሔድ ከገንዘብ፣ ከጊዜና ከቁሳቁስ አቅርቦት አንፃር አስቸጋሪ ስለሆነ አጥኚው አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም የሠሜን ወሎ ዞንን በናሙናነት መርጧል። ይህ ዞን የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው በዚህ ዞን ውስጥ ይሰራና ይማር ስለነበረ እንዲሁም ለጥናቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቂ መረጃዎች ይገኛሉ ብሎ ስላሰበ ነው።

3.1.2 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ይህ ጥናት በሠሜን ወሎ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ሀያ አንድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስቱን ትምህርት ቤቶች በተራ እጣ ናሙና ዘዴ መሰረት ተመርጠዋል። በጥናቱ

የተካተቱትም ሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው።

3.1.3 የመምህራን አመራረጥ

በሠሜን ወሎ ዞን ውስጥ ከተመረጡ ሶስት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ብዛት ዘጠኝ ሲሆን እነዚህም መምህራን በሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ አንድ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር፣ በቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሶስት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር እንዲሁም በወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አምስት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር ይገኛሉ። ነገር ግን እነዚህን መምህራን ካለው ጊዜ አንፃር በጥናቱ ውስጥ ለማካተት አስቸጋሪ ስለሆነ በሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህር አንድ ብቻ በመሆኑ እንዳለ በጥናቱ ሲካተት በቆቦና በወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በተራ የእጣ ናሙና ዘዴ አማካይነት ተመርጠዋል። በዚህም መሰረት በጥናቱ ውስጥ አምስት መምህራን በናሙናነት ተካተዋል።

3.1.4 የምድብና የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ አስራ ሰባት፣ በቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስራ አንድ እንዲሁም በሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሶስት በድምሩም 31 የዘጠነኛ ክፍል ምድቦች ይገኛሉ። ስለዚህ እነዚህን ምድቦች በጥናቱ ውስጥ ለማካተት አስቸጋሪ ስለሚሆን በወልዲያና በቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ምድቦችን በተራ የእጣ ናሙና ዘዴ 25% የሚሆኑት ተመርጠው በጥናቱ ውስጥ ተካተዋል። እንዲሁም በሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሶስት ምድቦች ብቻ በመሆናቸው እንዳለ በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል። በዚህ መሰረት በጥናቱ ውስጥ 10 የመማሪያ ክፍል ምድቦች ተመርጠዋል::

በናሙናነት ከተመረጡ ትምህርት ቤቶችና ምድቦች በመማር ላይ የሚገኙት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ ከ52-55 ተማሪዎች ይገኛሉ። ከእነዚህም መካከል በእያንዳንዱ ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍሎች ወላይ የሚሆኑ

ተማሪዎች በተራ የእጣ ናሙና ዘዴ አማካይነት 25% (134) የሚሆኑ ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል።

3.2 የጥናቱ መረጃ መሠብሠቢያ መሳሪያዎች

በዚህ ጥናት የሚካተቱ ትምህርት ቤቶች፣ የክፍል ደረጃ፣ የመምህራንና የተማሪዎች መረጣ ከተከናወነ በኋላ መረጃዎችን በተለያዩ ዘዴዎች አማካይነት የማሰባሰብ ስራ ተካሂዷል። ይህንን ለማድረግ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲሆን በአጋዥነት የመምህራን ቃለ መጠይቅና የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ጥቅም ላይ በመዋል መረጃዎች ተሰብስበዋል። የቃል መጠይቁ ለመምህራን የቀረበበት ምክንያት ቁጥራቸው አምስት በመሆኑና አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ያስችላል ተብሎ ስለታሰበ ነው።

3.2.1 ምልከታ

የክፍል ውስጥ ምልከታ የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ነው። ምልከታው የተካሄደው ውስን (fixed) የምልከታ ስልትን በመከተል ነው። በዚህ ውስን ምልከታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከሚከናወኑ ክንውኖች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች ቀደም ብሎ በተዘጋጀው የመከታተያ ቅፅ መከናወኑን ወይም አለመከናወኑን በማየት እንዲረጋገጥ ተደርጓል። የመከታተያ ቅፁ የተዘጋጀው ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ከተገለፀው ፅንሰ ሀሳብ በመነሳት ሲሆን ተግባራዊ ከመደረጉ በፊትም በአማካሪው ተገምግሞ እና አስተያየት ተሰጥቶበት አስፈላጊ ማሻሻያ ተደርጎበታል። /አባሪ አንድን ይመልከቱ/

የመከታተያ ቅፁን በመጠቀም በናሙናነት በተመረጡ ሶስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ አምስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በእያንዳንዳቸው ላይ ሶስት ሶስት ጊዜ ያህል የምልከታ ግምገማ ተካሂዷል። በምልከታ የተገኘውን መረጃ አስተማማኝነት ለማረጋገጥ ከአጥኚው በተጨማሪ አንድ በአማርኛ ቋንቋ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህር ምልከታው በሚከናወንባቸው ክፍሎች ውስጥ በመገኘት እገዛ አድርገዋል። ለአጋዥ መምህር ምልከታው ከመከናወኑ በፊት ከአጥኚው ጋር በቂ የጋራ ውይይት ከተደረገ በኋላ

ስለአሰራሩ መረጃ ተሰጥቷቸዋል። በዚህም መሰረት መረጃዎቹ ከተሰበሰቡ በኋላ ሁለቱ የምልከታ ውጤቶች ተደምረው አማካይ ውጤታቸውን በመውሰድ ለትንተና ቀርቧል።

3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቁ በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትግበራን አስመልክቶ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ ውሏል።ይህ የጽሑፍ መጠይቅ በቅድሚያ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ጥናቶች የተጠቀሙበትን መጠይቅ እንደ ሞዴል ተወስዶ ከጥናቱ ጋር እንዲስማ ሆኖ ተዘጋጅቷል። በመቀጠልም የጽሁፍ መጠይቁ በአማካሪዬ ተገምግሞና ማሻሻያ ተደርጎበት በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል። /አባሪ ሁለትን ይመልከቱ/

እንዲሁም የፅሁፍ መጠይቁ በተቻለ መጠን ግልጽ ቋንቋን ለመጠቀም ጥረት ከማድረጉም በላይ ተማሪዎች በርጋታ በማንበብ ተገቢ መረጃ ይሠጡ ዘንድ በቂ ጊዜ ተሠጥቷቸዋል። ይሁን እንጂ የፅሁፍ መጠይቁን ከሞሉት 134 ተማሪዎች መካከል ሶስቱ መጠይቁን ያልመለሱ ሲሆኑ ስድስቱ ደግሞ በትክክል ያልሞሉ በመሆናቸው ዘጠኝ ተማሪዎች ከጥናቱ ውጭ እንዲሆኑ በማድረግ ከ125 ተማሪዎች የተገኘው መረጃ ተተንትኖ ቀርቧል።

3.2.3 ቃለ መጠይቅ

ከጽሑፍ መጠይቅ እና ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅም የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ በመሆን አገልግሏል። ቃለ መጠይቁ በጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተዘጋጅቶ የቀረበ ሲሆን አላማውም መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ቅንጅታዊ በሆነ መንገድ እንዴት እያቀረቡ እንደሆነ፣ ስለቋንቋ ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤና የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ሲተገብሩ ስለሚገጥሟቸው ችግሮች መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በቃለ መጠይቁ የመምህራንን ዳራዊ መግለጫ አካቶ ይዟል። ቃለ መጠይቁም እንደ ምልከታና የጽሑፍ መጠይቁ ለጥናቱ እንዲስማ ሆኖ ከተዘጋጀ በኋላ በአማካሪዬ ተገምግሞና ማሻሻያ ተደርጎበት በግልጋሎት ላይ ውሏል። /አባሪ ሶስትን ይመልከቱ/ ቃለ መጠይቁ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ አጥኚው መቅረጽ ድምጽን (tape recorder) ተጠቅሟል።

3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ከክፍል ምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በማጠናቀር ለትንታኔ ቀርበዋል። በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች በመማር ማስተማር ሂደቱ መምህራን የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ምን እንደሚመስል በዝርዝር የሚያሳዩና አተገባበራቸውን የሚያመለክቱ በመሆናቸው የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክረዋል። በመሆኑም ትንተናው አሀዛዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በክፍል ምልከታውና በፅሁፍ መጠይቁ የተገኙት ውጤቶችን የድግግሞሽ መጠናቸው በመግለፅ በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ተተንትነዋል። በቃለ መጠይቅ አማካይነት የተገኙ መረጃዎች ደግሞ በምልከታ ለተገኘው መረጃ አጋዥ በመሆን ቀርበዋል።

ምዕራፍ አራት

የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ያቀርባሉ? ካቀረቡስ አቀራረቡ ምን እንደሚመስል አሀዛዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሞ በመተንተን ከውጤቱ መድረስ እንደሆነ በምዕራፍ ሶስት ላይ ተገልጿል።

የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢ መሳሪያዎች የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የተማሪዎቹ የጽሑፍ መጠይቅና መምህራን የጽሁፍ መጠይቅ እንደሆኑ በቀዳሚው ምዕራፍ ተጠቁሟል። አጥኚውም በእነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት መረጃዎችን ሰብስቧል። የዚህ ጥናት ክፍል ዓላማ ደግሞ ለተጠየቁት መሰረታዊ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው። ለዚህም በእንዳንዱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በዓላማዎቹ መሰረት እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል።

4.1 የተጠኚ መምህራን ዳራዊ መግለጫና የትምህርት ቤቶች አደረጃጀት

ሠንጠረዥ አንድ፡- የተጠኚ መምህራንና የትምህርት ቤቶች መግለጫን የሚያሳይ

ተ.ቁ	ትምህርት ቤቶች	የመምህራን ዳራዊ መግለጫ					
		መምህር	ጾታ	እድሜ	የትምህርት ደረጃ	የተመረቁበት መ.ያ	የአገልግሎት ዘመን
1	ሮቢት 2ኛ ደረጃ ት/ቤት	መ1	ወ	38	ዲግሪ	አማርኛ መምህር	12
2	ቆቦ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት	መ2	ወ	26	ዲግሪ	ጋዜጠኛ	3
		መ3	ሴ	33	ዲግሪ	አማርኛ መምህር	9
3	ወልዲያ2ኛ ደረጃ ት/ቤት	መ4	ሴ	30	ዲግሪ	እንግሊዝኛ መምህር	7
		መ5	ወ	29	ዲግሪ	አማርኛ መምህር	5

ከሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በጥናቱ በናሙናነት የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ሮቢት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ቆቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና ወልዲያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ በእንዳንዳቸውም የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ አምስት መምህራን የጥናቱ አካል ሆነዋል። ከእነዚህ መምህራን መካከል ሁለቱ ሴቶች ሲሆኑ ሶስቶቹ ደግሞ ወንዶች ናቸው። በተጨማሪም የመምህራን ዕድሜና የአገልግሎት ዘመን የተመለከትን እንደሆነ በመካከላቸው ልዩነት የሚታይባቸው ሲሆን የተመረቁበት የሙያ ዘርፍም ሶስቱ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር አንዷ ማለትም መ4 በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማር እና መ2 በጋዜጠኝነት ሙያ የሰለጠኑ እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል። በሌላ በኩል ሁሉም መምህራን በዲግሪ መርሀ ግብር ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ በመሆናቸው የትምህርት ደረጃቸው ተመሳሳይ ነው።

4.2 የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያለው እገዛ

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚቀርቡ ይዘቶች ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር ያላቸው አስተዋጾ ቀላል የሚባል አይደለም። ስለዚህ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች ረቂቅነታቸው ፣ ባህላዊ ገጽታቸው፣ የያዟቸው የመረጃ ብዛት፣ ድጋፍ ሰጪ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አቅርቦት አንጻር፣ የይዘቶቹ ስፋትና ስነ ልሳናዊ ክብደት ወዘተ. አንጻር ሊፈተሹ ይገባል። እንዲሁም የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማዳበርና ተማሪዎችን በተለያዩ ተግባራት ለማሳተፍ የሚያስችሉ ክንውኖችን ለማቅረብ የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል። ስለዚህ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶችን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኗል።

4.2.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜያት በአምስቱ መምህራን በተደረገው የሶስት ተከታታይ ምልከታዎች የቀረቡት ይዘቶች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ ሁለት፡- የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያለው እገዛ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የመከታተያ ነጥቦች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
1	የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ	-----	--	3	20	5	33.3	6	40	1	6.6
2	የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ያለው አስተዋጸ	---	--	2	13.3	5	33.3	6	40	2	13.3
3	የክፍለ ጊዜው ይዘት የመናገር ክሂልን ለማዳበር ያለው አስተዋጸ	---	--	3	20	4	26.6	5	33.3	3	20

ከላይ የቀረበው የምልከታ ሰንጠረዥ እንደሚያመለክተው በአምስት መምህራን በተደረገው 15 ተከታታይ ምልከታዎች ላይ የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ ምን እንደሚመስል ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ 3 (20%) ከፍተኛ፣ 5 (33.3%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 1 (6.6%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለማመልከት ተችሏል።

በ2ኛ ተራ ቁጥር የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና ምን ያህል እንደሆነ ለቀረበው ጥያቄ 2 (13.3%) ከፍተኛ፣ 5 (33.3%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 2(13.3%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለማየት ተችሏል። እንዲሁም በተራ ቁጥር 3 ለቀረበው

ጥያቄ 3 (20%)፣ ከፍተኛ፣ 4(26.6%) መካከለኛ፣ 5(33.3%) ዝቅተኛና 3(20%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለክታል።

ጠቅለል ባለ መልኩ የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያለው እገዛ ምን እንደሚመስል ለመመርመር በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

4.2.2 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ቃለ መጠይቅ የሚከተለው ምላሽ ሊገኝ ችሏል።

በተራ ቁጥር 10 ላይ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎቹን በተገቢው ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው እገዛ ምን ያህል ነው ? ለሚለው የቃል ጥያቄ ሶስቱ መምህራን ክሂሎቹን በቅንጅት ለማስተማርና ለማዳበር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ያላቸው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ሲገልጹ፣ ሁለቱ መምህራን ግን የሚያቀርቧቸው ይዘቶች በመማሪያ መጽሐፉ ወይም በመምህሩ መምሪያ ያሉትን እንደሆነ ከጠቀሱ በኋላ ይዘቶቹም የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማርና ለማዳበር ያላቸው እገዛ ዝቅተኛ እንደሆነ ገልጸዋል።

ከምልከታ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተኳሪ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎቹን በተገቢው ሁኔታ ለማቀናጀትና የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር ያላቸው እገዛ ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለክታሉ። (ሠንጠረዥ ሁለትን መመልከት ይቻላል)።

ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ሶስቱ መምህራን የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ክሂሎቹን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው እገዛ ከፍተኛ እንደሆኑ ቢገልጹም ተአማኒነት የለውም። ምክንያቱም በተካሄደው 15 ምልከታዎች ላይ የቀረቡት ይዘቶች 3 (20%) ብቻ የሆኑ ይዘቶች አስተዋጽኦቸው ከፍተኛ እንደነበር ለመረዳት ተችሏል።

በተለያዩ መርጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች የተገኙት ምላሾች ሲጠቃለሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቧቸው ይዘቶች

ክሂሎቹን በተገቢው ሁኔታ ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ በ4.2 ላይ የቀረቡት የትንተና ውጤቶች ያመለክታሉ።

4.3 የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወንና የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያለው አስተዋጸ

የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚቀርቡት ይዘቶች የክሂሎቹን ደረጃዎች ለመመተግበር፣ ንዑሳን ክሂሎችን ለማስተማር የሚያስችሉ፤ ከገሀዱ ዓለም ሀሳብ ልውውጥ ጋር በአቀራረባቸው የሚመሳሰሉ ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ገጠመኝና የክፍል ደረጃን ያገናዘቡ፤ ለውይይት የሚጋብዙ ሊሆኑ እንደሚገባ በተዛማጅ ጽሑፍ ቅኝት ውስጥ ተገልጽዋል። ስለዚህ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማስተማር የሚቀርቡትን ይዘቶች መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

4.3.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በተተኳሪ መምህራን አስራ አምስት ያህል ጊዜ በተካሄደው ምልከታ የቀረቡት ይዘቶች የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወንና የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ የሚከተለውን ይመስላል።

ሠንጠረዥ ሶስት፡- የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወንና የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ያላው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ

ተ.ቁ	የመከታተያ ነጥቦች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
4	የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥ ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወን ያለው ሚና	--	--	2	13.3	5	33.3	6	40	2	13.3
5	የክፍለ ጊዜው ይዘት የንግግር ደረጃዎችን ለማከናወን ያለው እገዛ	-	-	3	20	4	26.6	5	33.3	3	20
6	የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ገጠመኝና ችሎታ ጋር የመጣጣም ሁኔታ	--	--	4	26.6	4	26.6	5	33.3	2	13.3
19	ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ	--	--	3	20	4	26.6	7	46.6	1	6.6

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘው መረጃ በቁጥርና በመቶኛ ተቀምጧል። የተገኘው ውጤትም በሚከተለው መልኩ በትንተን ቀርቧል። በተራ ቁጥር 4 የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥ ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወን ያለው ሚና 2(13.3%)

ከፍተኛ፣ 5(33.3%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 2(13.3%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። በተመሳሳይ መልኩ በተራ ቁጥር 6 ላይ የክፍለ ጊዜው ይዘት የንግግር ደረጃዎችን ለማከናወን ያለው እገዛ ለማወቅ በተደረገው ለ15 ተከታታይ ምልከታዎች 3(20%) ከፍተኛ፣ 4(26.6%) መካከለኛ፣ 5(33.3%) ዝቅተኛና 3(20%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያመለክታል።

6ኛው የምልከታ ነጥብ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ገጠመኝና ችሎታ ጋር የመጣጣሙ ሁኔታ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ በተደረገው ተከታታይ ምልከታ 4(26.6%) ከፍተኛ፣ 4(26.6%) መካከለኛ፣ 5(33.3%) ዝቅተኛና 2(13.3%) በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ታውቋል። እንዲሁም በተራ ቁጥር 19 ላይ የክፍለ ጊዜው ይዘት ተማሪዎችን ምን ያህል ያሳትፋል? ለሚለው ጥያቄ 3(20%) ከፍተኛ፣ 4(26.6%) መካከለኛ፣ 7(46.6%) ዝቅተኛና 1(6.6%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ሊታወቅ ተችሏል።

ጠቅለል ባለ መልኩ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ገጠመኝና ችሎታ ጋር የማይጣጣሙና ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ለማሳተፍ ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ ነው። በተጨማሪም ይዘቶቹ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን በተሳካ መልኩ ለማቅረብ አመቺ እንዳልሆኑ ከላይ የቀረቡት የትንተና ውጤቶች ያስረዳሉ።

4.3.2 ከተማሪዎቹ የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ሠንጠረዥ አራት፡- የክፍለ ጊዜዎቹ ይዘት የመማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን ለማከናወንና የተማሪዎቹን ፍላጎት ለመማነሳሳት ያለው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የቀረቡ ጥያቄዎች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
13	የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች የክሂሎቹን ደረጃዎች ለመተግበር ያላቸው እገዛ	16	12.8	18	14.4	25	20	36	28.8	30	24
14	የማዳመጥና የመናገር ክሂልን መምህሩ/ሯ በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ከፍላጎትህ/ሽ፣ ከገጠመኝህ/ሽና ከችሎታህ/ሽ ጋር የተጣጣመ ናቸው	16	12.8	26	20.8	34	27.2	36	28.8	13	10.4

ከሰንጠረዡ እንደምንረዳው የማዳመትና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች ክሂሎቹን ደረጃዎች ለመተግበር ያላቸው እገዛ ምን ያህል ነው ለሚለው ጥያቄ 16 (12.8%) በጣም ከፍተኛ፣ 18 (14.4%) ከፍተኛ፣ 25 (20%) መካከለኛ ፣ 36 (28.8%) ዝቅተኛና 30 (24%) በጣም ዝቅተኛ የሆነ ምላሽ ሊገኝ ተችሏል። እንዲሁም በተራ ቁጥር 14 ለቀረበው ጥያቄ 16(12.8%) በጣም ከፍተኛ፣ 26(20.8%) ከፍተኛ፣ 34(27.2%) መካከለኛ፣ 36 (28.8%) ዝቅተኛና 13(10.4) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምልሽ ተሰጥቷል።

ከነዚህም ምላሾች እንደምንገነዘበው የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች የክሂሎቹን ደረጃዎች ለማዳበር ያላቸው እገዛ ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር ከተማሪዎች ችሎታ፣ገጠመኝና ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ እንዳልሆኑ ነው።

4.3.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

በዚህ ክፍል የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ዳራና ችሎታ ጋር የተዛመዱ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋሉ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁለቱ መምህራን የተማሪዎችን ዳራ ለመጠበቅ ተማሪዎቹ እነማን ናቸው? ከየት ነው የመጡት? ዕድሜያቸው? ወዘተ. የመሳሰሉትን ነጥቦች በማንሳት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ቅንጅታዊ ትምህርቱ የተማሪዎቹን ፍላጎት፣ ችሎታና ዳራ መሰረት ያደረገ እንዲሆን ጥረት እንደሚያደርጉ ሲገልጹ ሶስቱ መምህራን ግን የተማሪዎቹን ፍላጎት፣ ችሎታና ዳራ ሳይዳሰሱ እንዳለ በመማሪያ መጽሐፉ ያሉትን ይዘቶች እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል።

ከላይ ከምልከታ፣ ከተማሪዎች የጽሑፍና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘውን ምላሽ ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል። መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቡት ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ገጠመኝና ችሎታ ጋር የማይጣጣሙ እንዲሁም ተማሪዎችን ለማሳተፍ ያላቸው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ እንደሆነ ከምልከታና ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ያስረዳል። ከመምህራን የቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽም ሁለቱ መምህራን ብቻ ጥረት ማድረጋቸውን ሲገልጹ ቀሪዎቹ ሶስት መምህራን ግን ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረጋቸውን ገልጸዋል። የተማሪዎች ተሳትፎና ዳራ ደግሞ ለአንድ ትምህርት መሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ መኖሩን የዘነጉ ይመስላል።

4.4 የክፍለ ጊዜው ተግባራት (ክንውኖች) የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና

4.4.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

ሠንጠረዥ አምስት፡- የክፍለ ጊዜው ተግባራት (ክንውኖች) የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የመከታተያ ነጥቦች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
18	የክፍል ስራዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ብቃት	--	--	5	33.3	4	26.6	4	26.6	2	13.3
20	የቡድንና የጥንድ ውይይቶች የመናገርና የማዳመጥ ክሂልን የማጎልበት ብቃት	--	--	2	13.3	3	20	8	53.3	2	13.3
22	የቤት ስራዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና	--	--	1	6.6	3	20	9	60	2	13.3

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው የክፍል ስራዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸውን ብቃት ለመፈተሽ በተደረገው ተከታታይ ምልከታ የተገኘው ምላሽ 5(33.3%) ከፍተኛ፣ 4(26.6%) መካከለኛ፣ 4(26.6%) ዝቅተኛና 2 (13.3%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ነው።

ለ20ኛው የምልከታ ጥያቄ የተገኘው መረጃ 2(13.3%) ከፍተኛ፣ 3(20%) መካከለኛ፣ 8(53.3%) ዝቅተኛና 2(13.3%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ነው። እንዲሁም በተራ ቁጥር 22 ላይ የቤት ስራዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ምን ይመስላል ለሚለው ጥያቄ 1(6.6%) ከፍተኛ፣ 3(20%) መካከለኛ፣ 9(60%) ዝቅተኛና 2(13.3%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ከምልከታው የተገኘ ውጤት ያመለክታል።

ከነዚህም የምንረዳው የክፍል ስራዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው አስተዋፆ ከፍተኛ ቢሆንም የቤት ሥራዎችና የቡድን ውይይቶች ያላቸው ብቃት ዝቅተኛ እንደሆነ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂል ችሎታቸውን ያዳብራሉ ለማለት አያስደፍርም።

4.4.2 ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ የመረጃ ትንተና

ሰንጠረዥ ስድስት፡- የክፍለ ጊዜው ተግባራት (ክንውኖች) የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ምን እንደሚመስል ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የቀረቡ ጥያቄዎች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
1	ከክፍል ውጪ የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ዘገባዎችን በማዳመጥ መረጃዎችን እንድታሰባስብ/ቢ እና የጠየቅከውን/ሽውን ወይም ያሰባሰብከውን/ሽውን በክፍል ውስጥ እንድትወያዩባቸው የሚያደርጉ የቤት ስራዎችን	9	7.2	17	13.6	29	23.2	36	28.8	34	27.2

	መምህርህ/ሽ ይሰጣሉ?										
2	መምህርህ/ሽ የክፍል ስራዎችን እንድትሰራ/ሪ የሚጠይቁት ጥያቄዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን እንድታሳስበት/ቺና እንድትጠቀምበት/ሚበት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ	11	8.8	32	25.6	23	18.4	34	27.2	25	20

ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥ እንደሚያስረዱት በተራ ቁጥር አንድ ላይ ከክፍል ውጪ የተለያዩ ስራዎችን መምህርዎ ይሰጣሉ ለሚለው ጥያቄ 9 (7.2%) በጣም ከፍተኛ፣ 17 (13.6%) ከፍተኛ፣ 29(23.2%) መካከለኛ፣ 36(28.8%) ዝቅተኛና 34(27.2%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሊሰጡ እንደቻሉ ነው።

ለጥያቄ ሁለት ተማሪዎች 11(8.8%) በጣም ከፍተኛ፣ 32(25.6%) ከፍተኛ፣ 23(18.4%) መካከለኛ፣ 34(27.2%) ዝቅተኛና 25 (20%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ ምላሽ የሚያስረዳን መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያቀርቧቸው ጥቄዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማጎልበት ያላቸው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ እንደሆነ ነው።

4.5 መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችና ስልቶች

የቋንቋ ክሊሎች በቅንጅት በሚቀርቡበት ጊዜ ሃሳብን በቃል በማቅረብ፣ የፕሮጀክት ስራ በመስራት፣ ሚና ነጠቃ በማከናወን፣ ጌሞችን በመጫወት፣ እይታዊና ድምጻዊ መሳርያዎችን በመጠቀም እንዲያዳምጡ፣ ማስታወሻ እንዲይዙና ንግግር እንዲያደርጉ የሚጋብዙ የማስተማርያ ስልቶችን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በመጠቀም የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ማዳበር እንደሚቻል በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ላይ ተገልጽዋል።

በዚህ ክፍልም ተተኪ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሟቸውን ብልሃቶችና ስልቶችን ለማወቅ ከምልከታ፣ ከተማሪዎች የፅሁፍ

መጠይቅና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

4.5.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ስልቶችና ብልሃቶች ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ ሰባት፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ስልቶችና ብልሃቶች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የመከታተያ ነጥቦች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
10	ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክል እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ	-	-	3	20	5	33.3	7	46.6	-	-
11	ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲገልጹ ማድረግ	-	-	6	40	6	40	3	20	-	-
12	ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እንዲወያዩና እንዲከራከሩ የማድረግ ሁኔታ	-	-	2	13.3	4	26.6	6	40	3	20
13	የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን፣ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ምልልሶችንና ገለፃዎችን አዳምጠው ንግግር	-	-	2	13.3	1	6.6	10	66.6	2	13.3

	ወይም የሚና ክንውን እንዲያደርጉ የማስቻል ሁኔታ										
14	አንድን ፅሁፍ እንዲያዳምጡ ካደረጉ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲተርኩ የማድረግ ሁኔታ	-	-	2	13.3	4	26.6	6	40	3	20
15	ባዳመጡት ነገር ላይ ማጠቃለያ፣ ፍሬ ሀሳቡን (ጭብጡን) እና ለችግሮች መፍትሄ እንዲሰጡ የማድረግ ሁኔታ	-	-	3	20	5	33.3	6	40	1	6.6
16	የቀረበውን ይዘት ካዳመጡ በኋላ የይዘቱን ተገቢነት እንዲገመግሙ የማስቻል ሁኔታ	-	-	-	-	3	20	2	13.3	10	66.6

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክል እንዲገልፁ መምህራን በቂ ጊዜ የመስጠታቸው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለቀረበው ነጥብ 3(20%) ከፍተኛ፣ 5(33.3%) መካከለኛና 7(46%) ዝቅተኛ የሆነ ምላሽ ሊገኝ ተችሏል። በ11ኛው መከታተያ ነጥብ ተማሪዎች ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲመልሱ የሚያደርጉ ተግባራትን መምህራን ምን ያህል እንደሚሰጡ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ 6(40%) ከፍተኛ፣ 6(40%) መካከለኛና 3(20%) ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

በ12ኛው የምልከታ ነጥብ መምህራን ተማሪዎቹን በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እንዲወያዩና እንዲከራከሩ ያደርጋሉ ለሚለው ጥያቄ 2(13.3%) ከፍተኛ፣ 4(26.6%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 3(20%) በጣም ዝቅተኛ የሆነ ምላሽ ተገኝቷል።

በ13ኛው ጥያቄ መምህራን የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን፣ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ምልልሶችንና ገለፃዎችን ለተማሪዎች በማስደመጥ ንግግር ወይም የሚና ክንውን

እንዲያደርጉ የተጠቀሙት ክፍለ ጊዜያት 2(13.3%) ከፍተኛ፣ 1(6.6%) መካከለኛ፣ 10(66.6%) ዝቅተኛና 2(13.3%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

ለ14ኛው መከታተያ ነጥብ 2(13.3%) ከፍተኛ፣ 4(26.6%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 3(20%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ መምህራን ተማሪዎች አንድን ፁሁፍ እንዲያዳምጡ ካደረጉ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲተርኩ ማድረጋቸውን ለመገንዘብ ተችሏል።

በሰንጠረዡ ተራ ቁጥር 15 ተማሪዎች ባዳመጡት ነገር ላይ ማጠቃለያ፣ ጭብጡን (ፍሬ ሀሳቡን) ወይም ለችግሮች መፍትሄ እንዲሰጡ የሚያደርጉበት ጊዜ 3(20%) ከፍተኛ፣ 5(33.3%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 1(6.6%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ ማከናወናቸውን ያስረዳል።

በ16ኛው የምልከታ ነጥብ መምህራን የቀረበውን ይዘት ካዳመጡ በኋላ የይዘቱን ተገቢነት እንዲገመግሙ የሚደረግበት ጊዜያት 3(20%) መካከለኛ፣ 2(13.3%) ዝቅተኛና 10(66.6%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ታውቋል።

ከፍ ሲል ከመረጃ ትንተናው መረዳት እንደሚቻለው ተተኳሪ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ስልቶችና ብልሀቶች በተወሰኑ መምህራን ዘንድ ጥሩ ቢሆንም የአብዘሃኛዎቹ ግን ጥሩ የሚባል አይደለም። በተለይ ተማሪዎች የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን፣ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ምልልሶችንና ገለፃዎችን እንዲያዳምጡና ንግግር ወይም የሚና ክንውን እንዲያደርጉ የመጋበዝ ሁኔታ ሲታይ 66.6% የሚሆነው ዝቅተኛ ነው። በሌላ በኩልም የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የቀረበውን ይዘት ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ መምህራን ይዘቱን እንዲገመግሙ ያደርጋሉ ለሚለው ነጥብ 66.6% በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል።

በአጠቃላይ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶችና ስልቶች ለክሂሎቹ መዳበር ያለው አስተዋፆ ዝቅተኛ እንደሆነ ለመገንዘብ ተችሏል።

4.5.2 ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ሰንጠረዥ ስምንት፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ብልሀቶችና ስልቶች ምን እንደሚመስሉ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የቀረቡ ጥያቄዎች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
3	በክፍል ውስጥ ያዳመጥከውን/ሽውን ነገር በቃል እንድትመልስ/ሽ መምህርህ/ሽ ይጠይቃሉ?	20	16	31	24.8	35	28	23	18.4	16	12.8
4	የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን (ግጥም፣ ተውኔት፣ አጭር ልቦለድ ወዘተ.) በክፍል ውስጥ መምህርህ/ሽ በማምጣት እንድታዳምጥ/ጭ፣ እንድትወያይ/ዪ፣ መደምደሚያና ማጠቃለያ ሀሳብ እንድትሰጥ/ጭ ያደርጋሉ?	6	4.8	17	13.6	27	21.6	42	33.6	33	26.4
5	መምህርህ/ሽ አንድን ፅሁፍ ወይም ታሪክ እንድታዳምጥ/ጭ ካደረጉ በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ እንድትተርክ/ኪ ያደርጋሉ?	15	12	24	19.2	31	24.8	36	28.8	19	15.2
6	መምህርህ/ሽ በክፍል ውስጥ በቂ ጊዜ አግኝህ/ሽ እንድትነጋገር/ሪ	17	13.	29	23.2	28	22.4	30	24	21	16.8

	እድል ይሰጣሉ?		6								
8	መምህርህ/ሽ የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን፣ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ምልልሶችንና ገለፃዎችን በማቅረብ እንድታዳምጥ/ጭና ባዳመጥከው/ሽው መሰረት ንግግር ወይም የሚና ክንውን እንድታደርግ/ጊ ያግዙኋል/ሻል?	6	4.8	23	18.4	27	21.6	37	29.6	32	25.6
9	መምህርህ/ሽ በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ የቀደመ ዕውቀትህን/ሽን ለማስታዎስ በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ፍሬ ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ እንድትገምት/ቺና እንድትወይ/ዪ ያደርጋሉ?	21	16.8	34	27.2	32	25.6	27	21.6	11	8.8
10	እንድታዳምጥ/ጭ የቀረበልህን/ሽን የንግግር ይዘት ካዳመጥክ/ሽ በኋላ የይዘቱን ተገቢነት እንድትገመግም/ሚ የሚረዱ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ?	12	9.6	26	20.8	29	23.2	31	24.8	27	21.6
15	መምህርህ/ሽ በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እንድትወያይ/ዪ፣ እንድትከራከር/ሪና የቡድኑን ወይም የጥንዱን ሃሳብ አጠቃለህ/ሽ እንድትናገር/ሪ እድል ይሰጣሉ?	14	11.2	21	16.8	32	25.6	37	29.6	21	16.8

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ 3ኛው ጥያቄ በክፍል ውስጥ ያዳመጡትን ነገር ተማሪዎች በቃል እንዲመልሱ መምህራን ምን ያህል ጊዜ ይጠይቃሉ? ለሚለው ነጥብ ተማሪዎች 20(16%) በጣም ከፍተኛ፣ 31(24.8%) ከፍተኛ፣ 35(28%) መካከለኛ፣ 23(18.4%)

ዝቅተኛና 16(12.8%) በጣም ዝቅተኛ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ ምላሽ አብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲገልፁ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ ያስረዳል።

በ4ኛው ጥያቄ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን (ግጥም፣ ተውኔት፣ አጭር ልቦለድ ወዘተ.) በክፍል ውስጥ መምህርህ/ሽ እንድታዳምጥ/ጭና ባዳመጥከው/ው ነገር ላይ እንድትወያይ/ዪ፣ መደምደሚያና ማጠቃለያ ሀሳብ እንድትሰጥ/ጭ ያደርጋሉ? ለሚለው 6(4.8%) በጣም ከፍተኛ፣ 17(13.6%) ከፍተኛ፣ 27(21.6%) መካከለኛ፣ 42(33.6%) ዝቅተኛና 33(26.4%) በጣም ዝቅተኛ የሚላ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ ምላሽ የምንረዳው አብዛኛዎቹ መምህራን በክፍል ውስጥ የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን በማምጣት እንዲያዳምጡና ባዳመጡት ላይ እንዲወያዩ፣ መደምደሚያና ማጠቃለያ ሀሳብ እንዲሰጡ ሁኔታዎችን የማያመቻቹ እንደሆኑ ያስገነዝባል።

በ5ኛው ጥያቄ መምህርህ/ሽ አንድን ፅሁፍ ወይም ታሪክ እንድታዳምጥ/ጭ ካደረጉ በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ እንድትተርክ/ኪ ያደርጋሉ? ለሚለው 15(12%) በጣም ከፍተኛ፣ 24(19.2%) ከፍተኛ፣ 31(24.8%) መካከለኛ፣ 36(28.8%) ዝቅተኛና 19(15.2%) በጣም ዝቅተኛ የሆነ ምላሽ ሊሰጥ ተችሏል። ይህም ከምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር ሲነፃፀር እውነትነቱ ተቀባይነት ያለው ነው። እንዲሁም በተራ ቁጥር 6 ለቀረበው ጥያቄ 17(13.6%) በጣም ከፍተኛ፣ 29(23.2%) ከፍተኛ፣ 28(22.4%) መካከለኛ፣ 30(24%) ዝቅተኛና 21(16.8%) በጣም ዝቅተኛ በሆነ መልኩ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቂ ጊዜ አግኝተው እንዲነጋገሩ እድል መስጠታቸውን ያመለክታል። ምላሹም የሚያሳየው መምህራን ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ በቂ ጊዜ አለመስጠታቸውን ነው።

መምህርህ/ሽ የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን፣ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ምልልሶችንና ገለፃዎችን በማቅረብ እንድታዳምጥ/ጭና ባዳመጥከው/ሽው መሰረት ንግግር ወይም የሚና ክንውን እንድታደርግ/ጊ ያግዙኋል/ሻል? የሚል ጥያቄ በተራ ቁጥር 8 ላይ ቀርቦ 6(4.8%) በጣም ከፍተኛ፣ 23(18.4%) ከፍተኛ፣ 27(21.6%) መካከለኛ፣ 37(29.6%) ዝቅተኛና 32(25.6%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ እንደተገኘ ሰንጠረዥ ስምንት ያስረዳል። ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው መምህራን ይህንን ብልሀት አብዛኛውን ጊዜ እንደማይጠቀሙበት ነው።

መምህርህ/ሽ በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ የቀደመ ዕውቀትህን/ሽን ለማስታዎስ በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ፍሬ ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ እንድትገምት/ቺና እንድትወይ/ዪ ያደርጋሉ? ለሚለው ጥያቄ 21(16.8%) በጣም ከፍተኛ፣ 34(27.2%) ከፍተኛ፣ 32(25.6%) መካከለኛ፣ 27(21.6%) ዝቅተኛና 11(8.8%) በጣም ዝቅተኛ የሆነ ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህም የምንረዳው መምህራን ብልሃቱን አብዛኛውን ጊዜ ተግባራዊ እንደማያደርጉት ነው።

በተራ ቁጥር 10 ለቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ 12(9.6%) በጣም ከፍተኛ፣ 26(20.8%) ከፍተኛ፣ 29(23.2%) መካከለኛ፣ 31(24.8%) ዝቅተኛና 27(21.6%) በጣም ዝቅተኛ ያህል ጊዜ ተማሪዎች የሚቀረበላቸውን ይዘት ተገቢነት እንዲገመግሙ መደረጋቸውን ይገልፃል። እንዲሁም በተራ ቁጥር 15 ላይ መምህርህ/ሽ በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እንድትወያይ/ዪ፣ እንድትከራከር/ሪና የቡድኑን ወይም የጥንዱን ሃሳብ አጠቃለህ/ሽ እንድትናገር/ሪ እድል ይሰጣሉ? ለሚለው ጥያቄ 14(11.2%) በጣም ከፍተኛ፣ 21(16.8%) ከፍተኛ፣ 32(25.6%) መካከለኛ፣ 37(29.6%) ዝቅተኛና 21(16.8%) በጣም ዝቅተኛ የሆነ ምላሽ ሊሰጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ ከላይ የቀረበው ትንታኔ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችና ስልቶች የሚቀርበውን ይዘት ለተማሪዎች በማስተዋወቅና በርዕሱ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ፍሬ ሃሳቦችን እንዲገምቱ፣ እንዲወያዩና ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲገልፁ በማድረግ ሲሆን ሌሎች ብልሀቶችን በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተግባራዊ እንደማያደርጓቸው ያስረዳናል።

4.5.3 ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

በዚህ ክፍል መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸውን ብልሀቶች (ስልቶች) ለመፈተሽ የቃል መጠይቅ ለመምህራን ቀርቦ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በመማሪያ መፅሀፉ ያሉትን የማዳመጥና የመናገር መልመጃዎችን የሚያቀርቧቸው እንዴት ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሶስቱ መምህራን በመፅሀፉ ያሉትን መልመጃዎች ክሂሎቹን ለማስተማር ተስማሚ ስለሆኑ እንዳለ እንደሚያቀርቧቸው ገልፀዋል። ሁለቱ መምህራኖች ግን መሻሻል ያለባቸውን ነገሮች ካሉ እንደሚያሻሽሏቸው (በማቅለል፣ ግልፅ በማድረግ፣ በማክበድ) እንዲሁም ተማሪዎች ሰፋ ያለ ንግግር እንዳያደርጉ፣ እንዳይመራመሩና

እንዳያሰላስሉ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን በማስወጣት ሌላ ጥያቄዎችን ተክተው እንደሚያቀርቡ ገልፀዋል።

የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎች ቋንቋውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን እንዲገልፁና እንዲያዳምጡ ለማድረግ ምን አይነት ዘዴ ይጠቀማሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ አምስቱም መምህራን ተመሳሳይ የሆነ መልስ ሰጥተዋል። ይህም በመፅሀፉ ውስጥ የቀረበውን የማዳመጥና የመናገር ጥያቄዎችን በቃላቸው እንዲመልሱና አልፎ አልፎም በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ በማድረግ እንደሚያለማመዱ ገልፀዋል። አንደኛው መምህር ግን ከነዚህ በተጨማሪ ክርክርና የሚና ጨዋታዎችን እንደሚጠቀም ገልፀዋል።

ተማሪዎች ሰዎችን ጠይቀው ወይም ዜናዎችን፣ ውይይቶችን፣ ዘገባዎችን ወዘተ. . .አዳምጠው እንዲመጡና በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ የማድረግ ልምድ አለዎት? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሶስቱ መምህራን የማድረግ ልምድ እንዳላቸው ቢገልፁም አንዳንድ ጊዜ ካልሆነ በቀር ሁልጊዜ እንደማይተገብሩት ገልፀዋል። ሁለቱ መምህራን ግን ይህ አይነቱን ስልት እንደማይጠቀሙ ገልፀዋል። ሁለቱ መምህራን ላለመጠቀማቸውና ሶስቱ መምህራን ሁልጊዜ ተግባራዊ ላለማድረግ ያስቸገራችሁ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው መምህራን የሰጡት ምላሽ ተማሪዎች ይህን ተግባር እንዲያከናውኑ ብንሰጣቸውም እርስ በርስ ተነጋግረው (ተገለባብጠው) ስለሚመጡ፣ በተማሪዎች ላይ የቤተሰብ ጫና ስለሚኖርና ለማስቀረብ የጊዜ እጥረት ስለሚፈጥርባቸው እንደሆነ ገልፀዋል።

መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶችና ስልቶች ምን እንደሚመስሉ ለማወቅ በተደረገው ምልከታ፣ የፅሁፍና የቃል መጠይቅ የተገኙት ምላሾች ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል። ይኸውም ማዳመጥና መናገርን መምህራን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ አብዛኛውን ተግባራዊ የሚያደርጉት ተማሪዎች ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲገልፁ በማድረግ፣ አንዳንድ ጊዜ በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ ከማድረግ በዘለለ ሌሎች ብልሀቶችን እንደማይጠቀሙ ለማወቅ ተችሏል። ለአብነት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ምን አይነት ዘዴ ይጠቀማሉ? የቀረቡትን ተብለው መምህራን ለተጠየቁት የቃል ጥያቄ በመፅሀፉ ውስጥ የማዳመጥን የመናገር ጥያቄዎችን በቃላቸው እንዲመልሱና አልፎ አልፎም በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ በማድረግ

እንደሚያለማምዱ ምልሽ ሰጥተዋል። (4.5.3 ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘውን ምላሽ ይመልከቱ)

በአጠቃላይ ከዚህ የምንረዳው ክሂሎቹን አቀናጅቶ ለማስተማር የተለያዩ ብልሀቶችና ስልቶች ቢኖሩም መምህራን ግን ተማሪዎች ሃሳባቸውን በቃል እንዲገልፁ ከማድረግ በቀር ሌሎቹን ተግባራዊ እንደማያደርጉ ሊረጋገጥ ችሏል።

4.6 መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉት ጥረት

የማዳመጥና የመናገር ክሂል ተቀናጅተው እንዲቀርቡ ለማድረግ የመምህራን ሚና ወሳኝ ነው። የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማም የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት ማዳበር ማስቻል ነው። ለዚህ ደግሞ መምህራን የቡድንና የጥንድ ስራዎችን መስጠት፣ ተማሪዎች-እርስ በርስ እንዲወያዩ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡ በማድረግ፣ ከክፍል ተግባራት ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መፅሀፍትና ታሪኮችን ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ማንበብ፣ ንግግርን መምራት፣ የተለያዩ ቡድኖችን መመስረት፣ ምቹ የሆኑ የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ መገምገምና መቆጣጠር እንዲሁም ክሂሎቹን ለማቀናጀት የሚያግዙ መሳሪያዎችና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን መምረጥ፣ እየተጠቀመበት ያለው የአቀራረብ ዘዴ ክሂሎቹን ምን ያህል እያቀናጀ እንደሆነ መገምገም እንደሚኖርባቸው በተዛማጅ ፁሁፍ ቅኝት ውስጥ ተገልጿል። ስለዚህ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያደርጉትን ጥረት መፈተሽ አስፈላጊ ሆኗል።

4.6.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በአምስቱ መምህራን በተደረገው የሶስት የሶስት ተከታታይ ምልከታዎች መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉት ሚና ለማወቅ በተደረገው ምልከታ የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ ዘጠኝ፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉትን ጥረት ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የመከታተያ ነጥቦች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
7	መምህሩ/ሯ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከመማሪያ መፅሀፉ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ (ቴፕ ሪኮርደር፣ የመስክ ገ-ብኝት ወዘተ.) የመጠቀም ሁኔታ			2	13.3	3	20	8	53.3	2	13.3
8	ተማሪዎች እንዴት መናገርና ማዳመጥ እንዳለባቸው መመሪያ የመስጠት ሁኔታ			1	6.6	5	33.3	6	40	3	20
9	የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን የመተግበር ሁኔታ			3	20	6	40	5	33.3	1	6.6
17	ተማሪዎች በቋንቋው እንዲጠቀሙ የማበረታታት ሁኔታ			6	40	3	20	5	33.3	1	6.6
21	ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ዘገባዎችን እንዲሰበስቡና እንዲወያዩ የሚያደርግ የቤት ስራ የመስጠት ሁኔታ			1	6.6	3	20			11	73.3

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከመማርያ መጽሃፉ በተጨማሪ ሌላ የማስተማርያ መሳሪያ (ቴፕ ሪኮርደር፣ የመስክ ጉብኝት ወዘተ ...) የመጠቀም ሁኔታቸው ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ በተደረጉት 15 ምልከታዎች 2(13.3%) ከፍተኛ፣ 3(20%) መካከለኛ፣ 18(53.3%) ዝቅተኛ እና 2(13.3%) በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በተራ ቁጥር 8 መከታተያ ነጥብ ተማሪዎች እንዴት መናገርና ማዳመጥ እንዳለባቸው መምህራን መመሪያ የመስጠታቸው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ 1(6.6%) ከፍተኛ፣ 5(33.3%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 3(20%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል።

ለ17ኛው የምልከታ ነጥብ መምህራን ተማሪዎች በቋንቋው እንዲጠቀሙ የማበረታታቸው ሁኔታ 6(40%) ከፍተኛ፣ 3(20%) መካከለኛ፣ 5(33.3%) ዝቅተኛና 1(6.6%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

ለ9ኛው የመከታተያ ጥያቄ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን የተገበሩት ጊዜያት 3(20%) ከፍተኛ፣ 6(40%) መካከለኛ፣ 5(33.3%) ዝቅተኛና 1(6.6%) በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል። እንዲሁም በተራ ቁጥር 21 መምህራን ተማሪዎች ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ዘገባዎችን በማዳመጥ መረጃ እንዲሰበስቡና እንዲወያዩ የሚያደርጉ ተግባራትን የመስጠት ሁኔታን ለመፈተሽ በተደረገው ምልከታ 1(6.6%) ከፍተኛ፣ 3(20%) መካከለኛና 11(73.3%) በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያስረዳል።

ከፍ ሲል የመረጃ ጥንቅሩን በዝርዝር ለማቅረብ እንደተሞከረው ተተኳሪ መምህራን የማዳመጣና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ትምህርቱን የተሳካ ለማድረግ የሚያደርጉትን ጥረት ስንመለከት ዝቅተኛ እንደሆነ ነው።

በተለይ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከመማሪያ መጽሃፉ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ የመጠቀም ሁኔታና ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ዘገባዎችን በማዳመጥ መረጃ እንዲሰበስቡና እንዲወያዩ የሚያደርጉ የቤት ስራዎችን የስጠት ልምዳቸው ሲታይ ዝቅተኛ ነው።

4.6.2 ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ከላይ የቀረበውን የምልከታ ነጥብ ለማጠናከር ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ አስር፡- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉት ሚና ምን እንደሚመስል ከተማሪዎች የተገኘ ምላሽ

ተ.ቁ	የቀረቡ ጥያቄዎች	ድግግሞሽ									
		ሀ በጣም ከፍተኛ		ለ ከፍተኛ		ሐ መካከለኛ		መ ዝቅተኛ		ሠ በጣም ዝቅተኛ	
		በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%	በቁጥር	%
7	መምህርህ/ሽ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ሲያስተምሩ ከመማርያ መጽሃፉ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ (ቴፕ ሪኮርደር፣ የመስክ ጉብኝት፣ ወዘተ...) ይጠቀማሉ?	9	7.2	16	12.8	33	26.4	36	28.8	31	24.8
11	በንግግር ውስጥ የሚከሰቱ ምልክቶችንና አካላዊ ገለጻዎችን እንዴት መገንዘብ እንዳለብህ/ሽ መምህርህ/ሽ ያለማምዱሀል/ሻል?	13	10.4	24	19.2	26	20.8	40	32	22	17.6
12	ባዳመጥከው/ሽው መሰረት ንግግር ከማድረግህ/ሽ በፊት መምህርህ/ሽ የንግግር መመሪያን ያሳውቁሀል/ሻል?	18	14.4	21	16.8	28	22.4	35	28	23	18.4

በሰንጠረዥ ተራ ቁጥር 7 ላይ መምህርህ/ሽ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ሲያስተምሩ ከመማርያ መጽሃፉ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ (ቴፕ ሪኮርደር፣ የመስክ ጉብኝት፣ ወዘተ...) ይጠቀማሉ? ለሚለው ጥያቄ 9(7.2%) በጣም ከፍተኛ፣ 16(12.8%) ከፍተኛ፣ 33(26.4%) መካከለኛ፣ 36(28.8%) ዝቅተኛና 31(24.8%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ተማሪዎች ሰጥተዋል። ይህ ምላሽ ደግሞ የተወሰኑ መምህራን ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ የሆኑ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን እየተጠቀሙ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግን ተግባራዊ እንደማያደርጉ ያስረዳል።

ለ11ኛው ጥያቄ በንግግር ውስጥ የሚከሰቱ ምልክቶችንና አካላዊ ገለጻዎችን እንዴት መገንዘብ እንዳለብህ/ሽ መምህርህ/ሽ ያለማምዱሀል/ሻል? ለሚለው ነጥብ 13(10.4%) በጣም ከፍተኛ፣ 24(19.2%) ከፍተኛ፣ 26(20.8%) መካከለኛ፣ 40(32%) ዝቅተኛና 22(17.6%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ተማሪዎች ሰጥተዋል። ይህ ደግሞ ከምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር ሲነፃፀር ተመሳሳይነት ይታይበታል።

ተራ ቁጥር 12 ባዳመጥከው/ሽው መሰረት ንግግር ከማድረግህ/ሽ በፊት መምህርህ/ሽ የንግግር መመሪያን ያሳውቁሀል/ሻል? የሚል ጥያቄ ለተማሪዎች ቀርቦ 18(14.4%) በጣም ከፍተኛ፣ 21(16.8%) ከፍተኛ፣ 28(22.4%) መካከለኛ፣ 35(28%) ዝቅተኛና 23(18.4%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ከዚህ ምላሽ መረዳት የሚቻለው መምህራን ተማሪዎች ካዳመጡ በኋላ እንዴት መናገር እንዳለባቸው መመሪያ የማይሰጧቸው መሆኑን ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ትንታኔ መገንዘብ የሚቻለው የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር መምህራን ያለባቸውን ሀላፊነትና ሚና በአግባቡ እየተወጡ አለመሆናቸውን ነው፤

4.6.3 ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት የሚያደርጉትን ጥረት ለማወቅ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ በመሆኑ ከመምህራን የቃል መጠይቅ መረጃዎች ሊሰበሰብ ችሏል። የተገኘውም ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ በተማሪዎች ላይ የተመለከታቸው ድክመቶች አሉ? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ተማሪዎች በቡድንም ሆነ በጥንድ ለመወያየት ፍላጎት እንደሌላቸው፣ ለትምህርቱ ትኩረት እንደማያደርጉ፣ የቤት ስራዎችን በተገቢው እንደማይሰሩና ንግግር ለማድረግ እንደሚፈሩ ገልጸዋል። እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ምን አይነት መፍትሄ ይጠቀማሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ አንዱ መምህር ምንም አይነት መፍትሄ እንዳልተጠቀመ ከገለጸ በኋላ ለወደፊት ግን ከሙያ ባልደረቦቹ ጋር ውይይት በማድረግ መፍትሄዎችን እንደሚያፈላልግ አስገንዝቧል። ቀሪዎቹ አራት መምህራን ግን ለተማሪዎች የቡድንና የጥንድ ውይይት ያለውን ጠቀሜታ በማስገንዘብ ለማሳተፍ ጥረት እንደሚያደርጉ ፣ የቋንቋ ትምህርት ያለውን ጠቀሜታና ወደ ፊት በህይወታቸው ውስጥ ሊያገኙበት የሚያስችላቸውን አንዳንድ ነገሮችን የሰዎችን ታሪክ በምሳሌነት በማንሳት ለትምህርቱ ፍቅር እንዲኖራቸው እንደሚያደርጉና ፍራታቸውንም ለመቀነስ የተለያዩ ምክርና ማበረታቻ በመስጠት ችግሮቹን እየቀረፉ እንደሆነ ገልፀዋል።

ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥና መናገር እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጧቸዋል? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁሉም መምህራን መመሪያ እንደሚሰጡ ከገለፁ በኋላ ተማሪዎች ግን የሚሰጣቸውን መመሪያ እንደማይተገብሩት ሁለቱ መምህራን አስረድተዋል።

የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ትምህርቱን አስቸጋሪ የሚደርጉ ነገሮች አሉ? ካሉ ምንና ምን ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ችግሮች እንደሚገጥሟቸው ገልጸዋል።ችግሮቹንም ሲያብራሩ መማሪያ መፅሀፉ አብዛኛውን ጊዜ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማስተማር እንደማይጋብዝ፣ የክፍለ ጊዜና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጫና እንደሚፈጥሩባቸውና ለትምህርቱ የተመደበለት የጊዜ መጠን አናሳ መሆኑን ጠቁመዋል። ለነዚህ ችግሮች ምን አይነት አማራጭ መጠቀም ያስፈልጋል ብለው ያስባሉ? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ መማሪያ መፅሀፉ እንደገና ቢሻሻል፣ አስተዳደራዊ ጉዳዮች መፅሀፉ የግድ ማለቅ እንዳለበት ስለሚገልፁ ከመማሪያ መፅሀፉ በተጨማሪ ሌሎች ተግባራትን በተፈለገው አጋጣሚ እንዳንጠቀም ስላደረጉን ይህ ነገር ትኩረት ቢሰጠው፣ ለትምህርቱ የተመደበለት ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ ክሂሎቹን በተገቢው መንገድ ለማስተማር ስለማያስችል ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ቢመደብለት የተሻለ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

ከላይ በምልከታና በፁሁፍ መጠይቅ የተገኙት ምላሾች እንደሚያስረዱት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን የማቀናጀትና ትምህርቱን የተሳካ የማድረግ ሃላፊነታቸውን በአግባቡ

እየተወጡ እንዳልሆነ ነው። ምሳሌ በምልከታ ተራ ቁጥር 8 ላይ ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥና መናገር እንዳለባቸው መመሪያ የመስጠት ሁኔታ ለሚለው መከታተያ ነጥብ 1(6.6%) ከፍተኛ፣ 5(33.3%) መካከለኛ፣ 6(40%) ዝቅተኛና 3(20%) በጣም ዝቅተኛ የሚል ምለሽ ሊገኝ ችሏል። ከፀሁፍ መጠይቅ የተገኘው ውጤትም ከዚህ ጋር ሲነፃፀር ተመሳሳይ ሲሆን ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ግን በተወሰነ መልኩ ከላይ ከቀረበው ውጤት ጋር ይለያያል። ይህም ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥና መናገር እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጧቸዋል? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁሉም መምህራን መመሪያ እንደሚሰጡ ከገለፁ በኋላ ተማሪዎች ግን የሚሰጣቸውን መመሪያ እንደማይተገብሩት ሁለቱ መምህራን አስረድተዋል። ነገር ግን ለ15 ጊዜ በተካሄደው ምልከታ አንድ መምህር ብቻ መመሪያውን በቅድሚያ ሲያስተዋውቋቸው ተስተውሏል። ይህንም የተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ ይደግፈዋል።

በአጠቃላይ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ውስን መምህራን ትምህርቱ የተሳካ እንዲሆን ጥረት የሚያደርጉ ቢሆኑም አብዛኛዎቹ መምህራን ግን ሚናቸውን በአግባቡ እየተወጡ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል። ነገር ግን በተዛማጅ ቅኝት ፅሁፍ ላይ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማርና ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ ያላቸው ሚና ቀላል እንዳልሆነ ተገልጿል።

4.7 መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ

4.7.1 ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘ ምልሽ

የቋንቋ ክሂሎችን በቅንጅት ለማስተማር መምህራን የሚኖራቸው ግንዛቤና አመለካከት ለትምህርቱ ወሳኝነት አለው። ስለዚህ በዚህ ጥናት መምህራን ስለ ማዳመጥና መናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ መፈተሽ አስፈላጊ በመሆኑ ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ያስተምራሉ? ለሚለው ጥያቄ ሁሉም መምህራን ቀናጅተው እንደሚያስተምሩ ገልፀዋል። ለምን? ብሎ ለቀረበላቸው ክሂሎቹ በአብዛኛው ጊዜ

የማይነጣጠሉ በመሆናቸው እንደሆነ ገልፀዋል። አቀናጅተው በማስተማርዎ ደስተኛ ነዎት ለሚለው ሁሉም መምህራን ደስተኛ መሆናቸውን አስረድተዋል።

የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ በማስተማር ምን አይነት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለው ያስባሉ? ለሚለው ጥያቄ መ1፣ መ3 እና መ4 የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ከሌሎቹ ክሂል በበለጠ መልኩ ስለምንገለገልባቸውና ለሌሎቹ ክሂል መዳበር መሰረት ስለሆኑ እነዚህን ክሂሎች በቅንጅት በማስተማር የተማሪዎች ተግባቦት ብቃት ማሳደግ ይቻላል በማለት ያለውን ጠቀሜታ ገልፀዋል። መ5 ማዳመጥና መናገርን በቅንጅት ማስተማር ክሂሎቹ ተነጣጥለው እንዳይቀርቡ፣ ተማሪዎች እውናዊ የሆነውን የቋንቋ አጠቃቀም እንዲለማመዱና ትምህርቱን አዝናኝ በሆነ መልኩ ለማስተማር አመች መሆኑን ገልፀዋል። መ2 ግን ለቀረበላቸው ጥያቄ ምንም አይነት ምላሽ አልሰጡም።

ትምህርትዎን በሚማሩበት ጊዜ ወይም በተለያዩ ስልጠናዎችና ዎርክሾፖች ስለ ቋንቋ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንነትና ጠቀሜታ ተምረዋል (ተወያይተዋል)? ለሚለው ጥያቄ አራቱ መምህራን በአወንታ ሲመልሱ አንዱ መምህር ማለትም መ2 ግን ምንም አይነት ግንዛቤ እንደሌለው ገልጿል። ነገር ግን ሁሉም መምህራን በኮሌጅ ደረጃ በተማሩት እንጂ በስልጠናም ሆነ በዎርክሾፖች ላይ ለመካፈል አጋጣሚዎች እንዳልተፈጠሩላቸው አስረድተዋል።

4.8 የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ ያላቸው እገዛ

የመምህሩ መምሪያ መምህሩ የተማሪውን የመማሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊያስተምር እንደሚችል አቅጣጫ ጠቋሚ መሳሪያ ሲሆን የተማሪው መጽሀፍ ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲሠሩበት፣ የመማር ማስተማር ሂደቱን እንዲከታተሉበት የሚያስችል የማስተማሪያ መሳርያ ነው።

የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፍት የመማር ማስተማር ሂደትን የሚመሩ፣ የትምህርቱን መነሻና መድረሻ የሚጠቁሙ፣ የተለያዩ ይዘቶችን በምሳሌ አስደግፈው የሚያቀርቡ፣ መልመጃዎችና የተለያዩ ተግባራት በማቅረብ ተማሪዎችን እንዲለማመዱና የመማር ማስተማር ሂደቱን መረጃ የሚሠጡ እንደሆኑ በተዛማጅ ዑሁፍ ቅኝት ላይ

ተገልጿል።የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ ያላቸው አስተዋፆ ምን እንደሚመስል መፈተሽ አስፈላጊ ነው።

4.8.1 ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መጽሐፍ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ያላቸው እገዛ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከመምህራን የቃል መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ለክፍል ደረጃው የቀረበው የተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ ለማቅረብ አመቺ ነው? ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ አምስቱም መምህራን መጽሐፉ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማቅረብ የማይመች መሆኑን ገልፀዋል። ለምን? ለሚለው ነጥብ መጽሐፉ ለሁሉም ክሂሎች እኩል ትኩረት እንደማይሰጥና መልመጃዎቹ ተማሪዎቹን በተገቢው መልኩ ለማለማመድ የማያስችሉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የመምህሩን መምሪያ ይጠቀማሉ? ለሚለው ጥያቄ አራቱ መምህራን እንደሚጠቀሙ ገልፀዋል። የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብን ለመምራት ምን ያህል ጠቃሚ ነው? ለሚለው ነጥብ መምሪያው ከላይ በተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ ላይ እንደተገለፀው የማዳመጥና የመናገር ክሂል ይዘቶችን በስፋት አላካተተም። ነገር ግን በመጽሐፉ የቀረቡትን የማዳመጥና የመናገር ክሂል ይዘትና ተግባራትን ለመምራት፣ ለማቀድና ለመገምገም ምን አይነት ዘዴ ወይም ብልሀት መጠቀም እንዳለብን መነሻ ይሆናል በማለት ያለውን ጥቅም አብራርተዋል። አንዱ መምህር ግን በትምህርት ቤቱ የመምህሩ መምሪያ ስለሌለ እንደማይጠቀም ገልጿል። ለምን በአቅራቢያው ካሉ ትምህርት ቤቶች በመዋስ ወይም "ኮፒ" በማድረግ እንደማይጠቀም ለቀረበለት ጥያቄ ምንም አይነት ምላሽ አልሰጠም።

ምዕራፍ አምስት

ማጠቃለያ የመፍትሔ ሀሳብ

በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሰሜን ወሎ ዞን በተመረጡ ሶስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍለ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ያስተምራሉ? ካስተማሩስ ትምህርቱ ከክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ስነ ዘዴ አንፃር የለውን ተጣጥሞሽ በመፈተሽ በአተገባበሩ ላይ የማታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች መለየትና የታዩትን ደካማ ጎኖች የሚቀረፉባቸውን የመፍትሔ አቅጣጫዎች መጠቆም እንደሆነ ተገልጿል። በዚህም መሰረት በጥናቱ የተገኙት ውጤቶችና በጥናቱ ለተገኙት ችግሮች የመፍትሔ ሀሳብ በዚህ ክፍል ቀርቧል።

5.1. ማጠቃለያ

- በቋንቋ ማማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚቀርቡ ይዘቶች ክሂሎችን አቀናጅቶ ለማስተማር ያላቸው ሚና ቀላል የሚባል እንዳልሆነ ይታወቃል። ነገር ግን የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከሚያቀርቧቸው ይዘቶች የተወሰኑት ጥሩ የሚባል ቢሆኑም አብዛኛዎቹ መምህራን የማያቀርቧቸው ግን ክሂሎቹን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና ዝቅተኛ እንደሆነ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

- የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከሚቀርቡት ይዘቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ገጠመኝ፣ ችሎታ ጋር የማይጣጣሙና ተማሪዎቹን ለማሳተፍ የማያስችሉ መሆናቸውን የጥናቱ ግኝት ጠቁሟል።

- ክሂሎቹን ለማቀናጀትና ለማዳበር የሚቀርቡ የክፍል ውስጥ ተግባራት ያላቸው አስተዋፆ ጥሩ የሚባል ቢሆንም የቤት ሥራዎችና የቡድን ውይይቶች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማርና ለማዳበር የሚሰጡት ሚና ዝቅተኛ የሚባል እንደሆነ በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

- የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ ለማስተማር የሚያግዙ ስልቶች ሀሳብን በቃለ በማቅረብ፣ የፕሮጀክት ስራ በመስራት፣ የሚና ጨዋታ በማከሔድ የመረጃ

ክፍተትን በመሙላት፣ ተያያዥ ታሪኮችን በመናገር፣ ውይይት፣ ክርክር፣ ቃለመጠይቅ ወዘተ... በማድረግ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያግዙ ስልቶች ቢሆኑም አብዛኛዎቹ መምህራን ግን ተግባራዊ የማያደርጉት ስልት (ብልሀት) የሚደመጠውን ርዕሰ ጉዳይ ለተማሪዎች በማስተዋወቅ፣ በርዕሰ ጉዳዩ ሊነሱ የማችሉ ነገሮችን እንዲገምቱ፣ እንዲወያዩና ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲመልሱ በማድረግ እንደሆነ ጥናቱ ያመለክታል። ለዚህም መምህራን በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉት የማዳመጥና የመናገር መልመጃዎች ተማሪዎቹ ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲመልሱና አልፎ አልፎም በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ ብቻ ስለሚጋብዙ ሌሎች ብልሀቶችን ተግባራዊ የማያደርጉበትን ምክንያት ጠቁመዋል።

- የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግ የመምህራን ሚና ወሳኝ ነው። ስለዚህ ይህ ጥናት የተወሰኑ መምህራን ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥና መናገር እንዳለባቸው መመሪያ በመስጠት፣ ተማሪዎቹ በቋንቋው እንዲጠቀሙ በማበረታታት፣ ከመማሪያ መፅሀፉ በተጨማሪ ሌሎች የማስተማሪያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ወዘተ.. ትምህርቱን ስኬታማ ለማድረግና ክሂሎችን ለማቀናጀት ጥረት ሲያደርጉ አብዛኛዎቹ መምህራን ግን የሚጠበቅባቸውን ሚና በአግባቡ እየፈፀሙ እንዳልሆነ ለማወቅ ተችሏል።

- በዚህ ጥናት ውስጥ ከተገኙ ውጤቶች ውሰጥ አንዱ መምህራን ለማዳመጥና ለመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ነው። አብዛኛዎቹ መመህራን ስለማዳመጥና ስለመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ ጥሩ እንደሆነ ተስተውሏል። አንዱ መምህር ግን በጋዜጠኝነት ሙያ ስለተመረቀ ስለ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ምንም አይነት እውቀት እንደሌለው ለማወቅ ተችሏል። ነገር ግን እነዚህ መምህራን ስለክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ ያላቸው ግንዛቤ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የቀሰሙት እንጂ በተለያዩ ወርክሾፖችና ስልጠናዎች ላይ ያገኙት እንዳልሆነና ለወደፊት ግን በእንደነዚህ አይነት ስልጠናዎችና ውይይቶች ላይ በመሳተፍ የተሻለ ግንዛቤ ማግኘት እንደሚሹ ጥናቱ አረጋግጧል።

- ከፍ ሲል እንደተጠቆመው የተወሰኑት መምህራን አንዳንድ ጊዜ ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ የሚጠቀሙ ቢሆንም አብዛኛዎቹ መምህራን ግን በመማሪያ መፅሀፍ ውሰጥ ያሉትን ተግባራትና ይዘቶች ብቻ እንደሚጠቀሙ ተገልጿል።

- ስለዚህ የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መፅሀፍ የማዳመጥና የመናገር ክሂል በቅንጅት እንዴት መቅረብ እንዳለባቸውና ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት እንዲለማመዱ የማድረግ ብቃታቸው ጥሩ የሚባል ቢሆንም አንዳንድ ተግባራት ግን ክሂሎቹን ለማዳበር የሚያደረጉት አስተዋፅኦ አነስተኛና ወጥነት የጎደላቸው እንደሆኑ ጥናቱ ይጠቁማል።

በአጠቃላይ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አብዛኛወቹ መምህራን ትኩረት ሰጥተው በቅንጅት እንደማያቀርቧቸው ለማወቅ ተችሏል። በጥናቱ ውስጥም የታዩ ችግሮች፡- የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር የሚያስችሉ ይዘቶችን አለማቅርብ፤ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ዳራና ችሎታ አለመፈተሽ፤ ክሂሎችን ማዳበር የሚያስችሉ የቤት ስራዎችን አለመስጠት፤ ከመማሪያ መፅሀፉ ውጭ ለአላማው ተስማሚ የሆኑ ይዘቶችና ክንውኖችን በመምረጥ (በማዘጋጀት) አለመጠቀም፤ በተለያዩ ስልቶችና ብልሀቶች በመታገዝ ክሂሎቹን ለማቀናጀት አለመሞከር፤ የተማሪዎችን ውይይት አለመምራት(አለመቆጣጠር)፤ መማሪያ መፅሀፍ እንደብቸኛ ማስተማሪያ መሳሪያ አድርገው መጠቀም፤ መማሪያ መፅሀፉ ክሂሎቹ እኩል ሽፋን አለመስጠት የሚሉ ናቸው።

5.2. የመፍትሔ ሀሳብ

የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ችግር የሚፈጥሩና በመማር ማስተማሩ ሂደት አሉታዊ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ከዚህ በማስከተል በትምህርቱ ላይ ችግር ለሚፈጥሩና አሉታዊ ተፅእኖ ለሚያሳድሩ ነጥባች የመፍትሔ ሀሳብ ከዚህ በታች ቀርቧል።

- መመህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማርና ክሂሎቹን ለማዳበር የሚያግዙ ይዘቶችን ከመማሪያ መፅሀፉ በተጨማሪ በማዘጋጀት ወይም በመምረጥ እንዲሁም በመፅሀፉ ያሉትን ይዘቶች በማለዘብ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ቢያደርጉ።

- መምህራን የተማሪዎቹን ፍላጎት፣ ዳራና ችሎታ በመዳሰስ ከተማሪዎቹ ጋር ሊጣጣሙ የሚችሉ ተግባራትን በማዘጋጀት ቢያቀርቡ።

- የቋንቋ ትምህርት በክፍል ውስጥ ብቻ የሚካሔድ ስላልሆነ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት እንዲያዳብሩና እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ የቤት ስራዎችን መምህራን ቢሰጡና ቢከታተሉ።

- መምህራን የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት፣ ትምህርቱን አዝናኝ ለማድረግና የተማሪዎቹን ስሜት ለመግዛት የሚያስችሉ የተለየዩ የፈጠራ ስራዎችን በማምጣት ማወያየት፣ ማከራከር፣ ቃለ መጠይቅ፣ የሚና ጨዋታ፣ የመስክ ጉብኝት ወዘተ. በማድረግ የክፍል ውስጥ መስተጋብር መፍጠር ቢችሉ።

- መምህራን ተማሪዎች በቡድን በሚወያዩበት ጊዜ ምን እየሰሩ እንደሆነ በመቆጣጠርና ማስተካከያ በመስጠት ትምህርቱን ቢመሩ።

- የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ የተማሪዎቹን የተግባቦት ብቃት ማዳበር እስከ ሆነ ድረስ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ አዘጋጆች ክሂሎቹን በሚገባ የሚለማምዱና የሚያቀናጁ ይዘቶች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አካተው ቢያቀርቡ።

- መምህራን በመምህሩ መምሪያና በተማሪው መፅሀፍ ላይ ጥገኛ የመሆን ሁኔታ ስለታየ ለመምህራን ከእነዚህ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውጭ ሌሎች አጋዥ መሳሪያዎችን መጠቀም እንደሚችሉ ግንዛቤ የሚያገኙበት ስልጠና ቢሰጣቸው።

- የመምህሩ መምሪያና የተማሪው መፅሀፍ ለማዳመጥና ለመናገር ክሂል የሰጡት ሽፋን ዝቅተኛ ስለሆነ በአዲስ መልክ ተፈትሸው ሊሻሻሉ ይገባል

- መምህራንን የሚያሰለጥኑ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ስለ ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብና ጠቀሜታ ለሰልጣኝ መምህራን ሰፋ ያለ ትምህርት መስጠት ቢችሉ።

ዋቢ ጽሑፎች

አለም እሸቱ። (1995)። "በሁለተኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር"። አዲስ አበባ፣ ከጥቅምት 25-29/1995 ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጀ የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርቶችን ለማሻሻል የተዘጋጀ አውደ ጥናት የቀረበ (ከሥት/ዝ/ኝ/ም/ኢንስቲቲዩት)።

አለም እሸቱ። (1997)። *መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አታኻልቲ መኮንን። (1998)። "የቋንቋ ክሂሎችን አቀናጅቶ አማርኛን የማስተማር ዘዴ አተገባበር ፍተሻ።" አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለድህረ ምርቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ።

በድሉ ዋቅጅራ። (1996)። *በሰነፅሁፍ ቋንቋ ማስተማር*። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

በየነ ማሞ። (1986) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች ክሂሎችን ለማዳበር ያላቸው ሚና" አዲስ አበባ፣ ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ።

ዳንኤል ዘውዴና ሌሎች። (1994)። *የትምህርት ጥናትና ምርምር አተገባበር*። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ማረው አለሙ። (1998)። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*። አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

Allwright, D. (1998). *Observation in the Language Classroom*. London: Longman Group Ltd.

Anderson, A and Lynch, J. (1988). *Listing*. Oxford: Oxford University Press.

Atkins, J. et al. (1996). *Skills Development Methodology.* Part 2. Addis Ababa: Addis Ababa University Press.

Best, J. and Kahn, J. (2003). *Research in Education.* (7th ed.) New Delhi: Prentice Hall.

Brown, H. (1994). *Teaching by Principles: An Interactive Approach to Language Pedagogy.* New Jersey: Prentice Hall.

Byget, M. (1987). *Speaking.* London: Oxford University Press.

Byrne, D. (1981). *"Integrating Skill.* In Johnoson and Marrow. Hong Kong" Longman Group Ltd.

_____ (1986). *"Integrated skills." In teaching oral English* Hongkon: Longman Group Ltd.

_____(1987). *Techniques in Classroom Interaction Students,* Englewood Cliffs: MJ Prentice Hail.

Celce-murcia, M. (ed). (1991) *Teaching English as Second or Foreign Language.* Losangers. Heince and Hence Publishers.

Celce-murica, M. and Olshtain, E. (2000). *Discourse and Context in Language Teaching: A Guide for Language Teachers.* Cambridge: Cambridge University Press.

Cohen. L. et al. (2002). *Research Methods in Education.* New York: Goody by J.C Composition Ltd.

Cunningsworth, A. (1984). *Evaluating and Selecting English Foreign Language Teaching Materials.* London: Heinemann Educational Nooks.

Dale, P. and Wolf, J.C. (1988) Spech Communication for Interaction Students. Tesol Quarterly, 18(1), 41-45.

Ellis, R, (1984). *Classroom Second Language Development.* Oxford: Paragon Press Ltd.

Gilbert. J. (1982). Clear speech: Pronunciation and Listening Comprehension in English. *Tesol Quarterly.* Vol. 25 No. 1(Spring, 1991) pp.51-75

Gower, et al. (1995). *Teaching Practice Hand Book.* Great Britain: The Bath press.

Grant, N. (1989). *The Most of Your Text Book.* New York: Longman Group Ltd.

Harmer, J. (1991). *The Practice of English Language Teaching.* London: Longman Group Ltd.

Hill. J. (1986). *Using Literature in Language Teaching.* London. Macmillan Publisher Ltd.

Krashen, D. S. (1981). *Principle and practice in second language aquation.* Britain: Prentice Hall International.

Littilewood, W. (1981). *Communicative Language Teaching.* Cambridge: Cambridge University Press.

Marey, A. and Sandra, M. (1981). *Learning to Listen: Tasks or Developing Listening Skill.* Cambridge: Cambridge University Press.

McDonough, J and Shaw. C. (1992). *"Integrated Skills. In Elt A Teachers Guide.* Oxford: Blackwell.

_____ (1993). *Materials and Methods in ELT. A Teachers Gide.* Oxford: Black Well.

Nunan, D. (1994). *Designing Tasks for Communicative Classroom* Cambridge: Cambridge University Press.

Oxford, R, (2001). "Integrated skills in the ELS/EFL Clasroom". *ERIV. Maio: eric@cas.org*.

Richards, J. and Rodgers. J. (1986). *Approaches and methods in Language teaching*. Cambridge: Cambridge University Press.

Rivers, W. (1981). *Teaching Foreign Language Skills*. Chicago: Cicago university press.

Rixo, A. (1986). *Developing Listening Skills*. London: Macmillan Publisher Ltd.

Sheal, P. (1989). "Class Room Observation Training the Observers" in *ELT. Journal* Volume 43/2 London: Oxford University.

Snow; B. G and perkins, K. (1979). The Teaching of Listening Comprehension and Communication Activities. *TESOL Ounortery, 13 (1), 51-63.*

Stern, S. (1991). "An Integrated Approach to Literature in ESL/EFL pp. 328-345: In Celce-murcial. *Teaching English as Secondary or Foreign Language.* Losngleos: Heince and Henice Publishers. ›

Tylor, H. M. (1981). Learning to Listen to English. TESOL Quartery, 15(1), 41-550.

Underwood (1989). *Teaching listening*, London: Longman Group Ltd.

Ur,p. (1990). *Teaching Listening comprehension.* New York: Cambridge: Cambridge University press.

_____ (1996). *A Course in Language Teaching: Practice and theory*. Cambridge: Cambridge University Press.

Widdowson, H. (1990). *Aspects of Language Teaching*. Oxford: Oxford University Press.

አባሪ አንድ

የክፍል ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥና የንግግር ክሂል ቅንጅታዊ ትምህርት አቀራረብ መረጃ መሠብሰቢያ ቅጽ (check list)

ምልከታ _____ ቀን ---- ወር ------ አመት --------

የትምህርት ቤቱ ስም _____ ትምህርቱ የተጀመረበት ጊዜ ---------

ሴክሽን---------- ትምህርቱ የተጠናቀቀበት ጊዜ -------

ክፍለ ጊዜ _____ የተማሪ ብዛት ----------

የእለቱ የትምህርት ርዕስ _____

የእለቱ የትምህርት አላማ(ዎች) _____

_____

_____

መልሱን የ(√) ምልክት በማድረግ ማሳየት።

መስፈርቶቹ፡- ሀ. በጣም ከፍተኛ ሐ. መካከለኛ ሠ. በጣም ዝቅተኛ

ለ. ከፍተኛ መ. ዝቅተኛ

ተቁ	መከታተያ ነጥብ	ሀ	ለ	ሐ	መ	ሠ
1	የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀት ያለው እገዛ					
2	የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥ ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና					
3	የክፍለ ጊዜው ይዘት የመናገር ክሂልን ለማዳበር ያለው ሚና					
4	የክፍለ ጊዜው ይዘት የማዳመጥ ክሂል					

	ደረጃዎችን ለማከናወን ያለው ሚና					
5	የክፍለ ጊዜው ይዘት የንግግር ደረጃዎችን ለማከናወን ያለው እገዛ					
6	የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርበው ይዘት ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ገጠመኝና ችሎታ ጋር የመጣጣም ሁኔታ					
7	መምህሩ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር ከመማሪያ መፅሀፉ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ (ቴፕ ሪኮርደር፣የመስክ ጉብኝትወዘተ) የመጠቀም ሁኔታ					
8	ተማሪዎች እንዴት መናገርና ማዳመጥ እንዳለባቸው መመሪያ የመስጠት ሁኔታ					
9	የማዳመጥና የመናገር ክሂል ደረጃዎችን የመተግበር ሁኔታ					
10	ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክል እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ					
11	ያዳመጡትን ነገር በቃል እንዲገልጹ ማድረግ					
12	ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እንዲወያዩና እንዲከራከሩ የማድረግ ሁኔታ					
13	የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን፣ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ምልልሶችንና ገለፃዎችን አዳምጠው ንግግር ወይም የሚና ክንውን እንዲያደርጉ የማስቻል ሁኔታ					
14	አንድን ፁሁፍ እንዲያዳምጡ ካደረጉ በኋላ					

	ለክፍል ጓደኞቻችው እንዲተርኩ የማድረግ ሁኔታ					
15	ባዳመጡት ነገር ላይ ማጠቃለያ፣ ፍሬ ሀሳቡን (ጭብጡን) እና ለችግሮች መፍትሄ እንዲሰጡ የማድረግ ሁኔታ					
16	የቀረበውን ይዘት ካዳመጡ በኋላ የይዘቱን ተገቢነት እንዲገመግሙ የማስቻል ሁኔታ					
17	ተማሪዎች በቋንቋው እንዲጠቀሙ የማበረታታት ሁኔታ					
18	የክፍል ስራዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ብቃት					
19	ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ					
20	የቡድንና የጥንድ ውይይቶች የመናገርና የማዳመጥ ክሂልን የማጎልበት ብቃት					
21	ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ዘገባዎችን እንዲሰበስቡና እንዲወያዩ የሚያደርግ የቤት ስራ የመስጠት ሁኔታ					
22	የቤት ስራዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ለማቀናጀትና ለማዳበር ያላቸው ሚና					

23. አጠቃላይ በመማር ማስተማር ሂደቱ የማዳመጥና የንግግር ክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ አጠር ያለ ግለዊ አስተያየት _____

_____

_____

_____

አባሪ ሁለት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

በ2003 ዓ.ም. አንደኛ ወሠነ ትምህርት በተመረጡ በሠሜን ወሎ ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪ ሆይ፡

በመጀመሪያ ክቡር ጊዜህን/ሽን መስዋዕት በማድረግ ይህን መጠይቅ ለመሙላት ፈቃደኛ በመሆንህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ።

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ፡- የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማዳመጥና የንግግር ክሂልን ትኩረት ሠጥተው አቀናጅተው ያቀረቡ እንደሆነ መፈተሸና በአቀራረቡ የታዩትን ችግሮች መርምሮ መፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ለታቀደው ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው። ጥናቱ ከተፈለገው ግብ እንዲደርስም ተገቢ መረጃዎችን ማጠናከርን ይፈልጋል። በመሆኑም ከጥናቱ ተገቢ አስተያየት እንዲገኝ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በእርጋታ በማንበብ መልስህን/ሽን በማያሻማ መልኩ በተሠጠው ቦታ ላይ እንድታሰፍር/ሪ በትህትና እጠይቃለሁ።

ማሳሰቢያ፡-

ሀ. በመጠየቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም

ለ. ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የአንተ/ቺ ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው።

ሐ. የመጠይቁን ጥያቄዎች ከሌሎች ሠዎች ጋር በመመካከር ቢሞላ በጥናቱ ውጤት ላይ ተፅእኖ ስለሚያሳድር ብቻህን/ሽን መላ/ዪ።

መ. ከተነሱት ጥያቄዎች ተጨማሪ ሀሳብ ካለህ/ሽ በመጠይቁ መጨረሻ ላይ ማስፈር ትችላለህ/ለሽ።

ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ መረጃ

1. የትምህርት ቤቱ ስም _____
2. ፆታ _____
3. እድሜ _____
4. ሴክሽን _____

ክፍል ሁለት

መመሪያ፡- ከዚህ በታች የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥና ንግግር ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብን የሚያመለክቱ ሀተታዎች ቀርበዋል። የትግበራ አይነቶች ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆኑ ከተሠጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን መልስ ይሂል የሚሉትን ሆሄ በመምረጥ በሠንጠረዡ ካሉት ሆሄያት ሥር የ(√) ምልክት ያስቀምጡ። አማራጮቹም

ሀ. ሁል ጊዜ ሐ. በመጠኑ ሠ. በጭራሽ አይደረግም

ለ. አብዛኛውን ጊዜ መ. አንዳንድ ጊዜ

የሚሉትን አማራጮችን ይወክላሉ።

ተ.ቁ	ጥያቄዎች	ሀ	ለ	ሐ	መ	ሠ
1	ከክፍል ውጪ የተለያዩ ሰዎችን በመጠየቅ ወይም ዘገባዎችን በማዳመጥ መረጃዎችን እንድታሰባስብ/ቢ እና የጠየቅከውን/ሽውን ወይም ያሰባሰብከውን/ሽውን በክፍል ውስጥ እንድትወያዩባቸው የሚያደርግ የቤት ስራዎችን መምህርህ/ሽ ይሰጣሉ?					
2	መምህርህ/ሽ የክፍል ስራዎችን እንድትሰራ/ሪ የሚጠይቁት ጥያቄዎች የማዳመጥና የመናገር ክሂልን እንድታጎለብት/ቺና እንድትጠቀምበት/ሚበት					

	ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ					
3	በክፍል ውስጥ ያዳመጥከውን/ ሽውን ነገር በቃል እንድትመልስ/ሽ መምህርህ/ሽ ይጠይቃሉ?					
4	የተለያዩ የፈጠራ ስራዎችን (ግጥም፣ ተውኔት፣ አጭር ልቦለድ ወዘተ.) በክፍል ውስጥ መምህርህ/ሽ በማምጣት እንድታዳምጥ/ጭ፣ እንድትወያይ/ዪ፣ መደምደሚያና ማጠቃለያ ሀሳብ እንድትሰጥ/ጭ ያደርጋሉ?					
5	መምህርህ/ሽ አንድን ፅሁፍ ወይም ታሪክ እንድታዳምጥ/ጭ ካደረጉ በኋላ ለክፍል ጓደኞችህ/ሽ እንድትተርክ/ኪ ያደርጋሉ?					
6	መምህርህ/ሽ በክፍል ውስጥ በቂ ጊዜ አግኝህ/ሽ እንድትነጋገር/ሪ እድል ይሰጣሉ?					
7	መምህርህ/ሽ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅተው ሲያስተምሩ ከመማርያ መጽሃፉ በተጨማሪ ሌላ የማስተማሪያ መሳሪያ (ቴፕ ሪኮርደር፣ የመስክ ጉብኝት፣ ወዘተ...) ይጠቀማሉ?					
8	መምህርህ/ሽ የተለያዩ አጫጭር ታሪኮችን፣ በሰዎች መካከል የሚደረጉ ምልልሶችንና ገለፃዎችን በማቅረብ እንድታዳምጥ/ጭና ባዳመጥከው/ሽው መሰረት ንግግር ወይም የሚና ክንውን እንድታደርግ/ጊ ያግዙኋል/ሻል?					
9	መምህርህ/ሽ በቅድመ ማዳመጥ ጊዜ የቀደመ ዕውቀትህን/ሽን ለማስታዎስ በርዕሱ ዙሪያ ምን ምን ፍሬ ሀሳቦች ሊነሱ እንደሚችሉ እንድትገምት/ቺና					

	እንድትወይ/ዪ ያደርጋሉ?					
10	እንድታዳምጥ/ጭ የቀረበልህን/ሽን የንግግር ይዘት ካዳመጥክ/ሽ በኋላ የይዘቱን ተገቢነት እንድትገመግም/ሚ የሚረዱ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ?					
11	በንግግር ውስጥ የሚከሰቱ ምልክቶችንና አካላዊ ገለጻዎችን እንዴት መገንዘብ እንዳለብህ/ሽ መምህርህ/ሽ ያለማምዱሀል/ሻል?					
12	ባዳመጥከው/ሽው መሰረት ንግግር ከማድረግህ/ሽ በፊት መምህርህ/ሽ የንግግር መመሪያን ያሳውቁሀል/ሻል?					
13	የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚቀርቡ ይዘቶች የክሂሎቹን ደረጃዎች ለመተግበር ያላቸው እገዛ					
14	የማዳመጥና የመናገር ክሂልን መምህሩ/ሯ በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ከፍላጎትህ/ሽ፣ ከገጠመኝህ/ሽና ከችሎታህ/ሽ ጋር የተጣጣሙ ናቸው					
15	መምህርህ/ሽ በቡድንና በጥንድ በማደራጀት እንድትወያይ/ዪ፣ እንድትከራከር/ሪና የቡድኑን ወይም የጥንዱን ሃሳብ አጠቃለህ/ሽ እንድትናገር/ሪ እድል ይሰጣሉ?					

ተጨማሪ አስተያየት ካለህ/ሽ ከዚህ በታች ያለውን ክፍት ቦታ ተጠቀም/ሚ

አባሪ ሶስት

ለዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚቀርቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

ክፍል አንድ ፦ የመምህራን አጠቃላይ መረጃ

1. ፆታ _____

2. እድሜ __

3. የትምህርት ደረጃ _____

4 .የተመረቁበት የትምህርት አይነት _____

5. የአገልግሎት ዘመን _____

ቋንቋን በማስተማር ልዩ ስልጠና ወስደው ከሆነ በምን ይግለፁ _____

ክፍል ሁለት፦ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ቅንጅታዊ አተገባበር የተመለከተ ጥያቄ

1. የማዳመጥና የንግግር ክሂልን አቀናጅተው ያስተማራሉ? ለምን?
2. ማዳመጥና ንግግር ክሂልን አቀናጅተው ለማስተማር ደስተኛ ነዎት? ለምን?
3. የማዳመጥንና የንግግርን ክሂልን በሚያስተምሩበት ጊዜ በተማሪዎች ላይ የተመለከቷቸው ድክመቶች አሉ? ድክመቶቹንስ ለማሻሻል ምን አይነት መፍትሄ ይጠቀማሉ?
4. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉትን የማዳመጥና የንግግር መልመጃዎች የሚቀርቧቸው እንዴት ነው? ለምን?
5. የተማሪው መፅሐፍ የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ ለማቅረብ አመቺ ነው? የእርስዎስ የአቀራረብ ስልትስ ምን ይመስላል?
6. የማዳመጥና የመናገር ክሂልን አቀናጅቶ ማስተማር ምን አይነት ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለው ያስባሉ?
7. የመምህሩን መምሪያ ይጠቀማሉ? የማዳመጥና የመናገር ክሂልን ቅንጅታዊ ትምህርት ለመምራት ምን ያህል ጠቃሚ ነው?

8. የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎች ቋንቋውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን እንዲገልፁና እንዲያዳምጡ ለማድረግ ምን አይነት ዘዴ ይጠቀማሉ? ለምን? እንዴት?

9. ተማሪዎች ሰዎችን ጠይቀው ወይም ዜናዎችን፣ ውይይቶችን፣ ዘገባዎችን ወዘተ አዳምጠው በክፍል ውስጥ እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ የማድረግ ልምድ አለዎት? ከሌዎት ችግሩ ምንድን ነው?

10. የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት ለማስተማር የሚያቀርቧቸው ይዘቶች ከተማሪዎች ፍላጎት፣ ዳራ፣ ችሎታ ጋር የተዛመዱ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጋሉ?


11. ተማሪዎች እንዴት ማዳመጥና መናገር እንዳለባቸው መመሪያ ይሠጧቸዋል?

12. የማዳመጥና የመናገር ክሂልን በቅንጅት በሚስተምሩበት ጊዜ ትምህርቱን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ነገሮች አሉ? ካሉስ ምን አይነት ነገሮች ናቸው? ለነዚህስ ምን አይነት አማራጭ መጠቀም ያስፈልጋል ይላሉ?

ክቡር መምህር ሆይ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የማዳመጥና የመናገር ክሂል ትኩረት ተሰጥተው ይቀርቡ እንደሆነና በአቀራረቡ የሚታዩ ችግሮች ካሉ መርምሮ መፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም በተደረገው ጥናት ጊዜዎን መስዋት በማድረግ ይህንን ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ፈቃደኛ በመሆንዎ ከልብ አመሰግናለሁ።

በጥናቱ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ጥላሁን ከበደ

ፊርማ፡- 

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

ቀን፡- ጥር 2003 ዓ.ም